ጤና ይስጥልኝ፤ ፈረንጅኛውን ለምትቆጥሩ መልካም አዲስ ዓመትና ፍሬያማ 2012 እመኝላችኋለሁ። እንኳን ለብርሃነ ልደቱ በሰላም አደረሰን።

በዚህ የዕዝራ ስርጭት

<u>ፕሮቴስታንታዊ ጅሃድ</u> በሚል ርእስ የተዘጋጀና የተሰራጨ ዲቪዲ ነበረ። በYouTube ላይም የዲቪዲው አጫጭር ቁራጮች በተለያዩ ምንጮች ተኮልኩለዋል። ዲቪዲው በፓስተር ዳዊት ስብከት ላይ የተሰጠ ምላሽ ቢሆንም በነገረ ማርያም ላይ ያተኮረ ነው። ይህ መጣጥፍ በ3 ክፍል የተሠራው ክፍል አንድ ሆኖ የመልሱ ምላሽ ሳይሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ማርያም በእርግጥ ማን መሆኗን የሚያመለክት ነው። የተፈጠሩ ተረቶችን ሳይሆን ቃሉን ነው ማንበብና መቀበል ያለብን።

ጌታ ቢፈቅድና ብንኖርም በሁለተኛውም ይኸው ይቀጥልና በመጨረሻው ደግሞ ተአምረ ማርያም የተሰኘውን መጽሐፍ በጥቂቱ እንቃኛለን።

## ፕሮቴስታንታዊ ጅሃድ? ? ?



በሁለተኛው <u>እንደሚገባ ኑሩ</u> በሚል የጳውሎስን መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች ጥናት እንቀጥላለን። የተጠራንበትና መዳናችን የታወጀልን ወንጌል የከበረ ወንጌል ነው፤ ታዲያ የዚያኑ ያህል የእኛም ኑሮ ያንን ያንጸባረቀ መሆን ይገባዋል። የተገባው ነውና እንደሚገባ ልንኖር ተጠርተናል።

## እንደሚገባ ኑሩ

በሦስተኛው <u>የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ</u> በሚል ርእስ ስለ ጌታችን ልደተ ሥጋ በማገለግልባት ቤተ ክርስቲያን በዚህ የልደት ሰሞን ያካፈልኩትን ለጽሑፍ እንዲመች አድርጌ አቅርቤዋለሁ።

## የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ

መልካም ንባብ።

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ፥ ዘላለም መንግሥቱ





# ፕሮቴስታንታዊ ጅሃድ???

**ማርያም እግዝእት ናትን? ማርያም ልጆች ነበሩአት ወይስ አልነበሩአትም? ወላዲተ አምላክ ምን ማለት ነው? ማርያም ታማልዳለችን? የሕዝቅኤል የተዘጋው በር ማርያም ናትን? ቤዛዊተ ኩሉ ዓለምስ ናትን? ተአምረ ማርያም ምንድር ነው? መቼ ተጻፈ? ማን ጻፈው? ከየት ተገኘ? መቼ ተተረጎመ?**

## ክፍል አንድ

ከጥቂት ወራት በፊት አንዲት ትንሽ የዩቱብ ቪዲዮ ቁራጭ እንድመለከት ተልካልኝ አየሁ። መጋቢ ዳዊት ሞላልኝ በአንድ ሁለት ስብከቶች ላይ ከሰበካቸው ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ - ነክ ቃላት ላይ የተሰጠ ምላሽ ነበረ። ግን እንዳልኩት ስብከቱም ምላሹም ቁራጭ ብቻ ነበረ። በቅርብ አንድ ወንድም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመ/ር ምህረተአብ አሰፋ አማካይነት ተዘጋጅቶና ተቀናብሮ የተሰራጨ ምላሽ ላከልኝ። በዚህኛው ምላሹ ሙሉና የተቀነባበረ ሲሆን የመጋቢ ዳዊት ስብከት አሁንም ምላሽ ሊሰጥበት ተፈልጎ የተወሰደው ቅንጣቢ ይህን የምጽፈው በምላሹ ላይ ጥቂት ልጽፍ ፈልጌ ነው። የምጽፈው በመላው ምላሹ ሳይሆን በሁለት ነጥቦች ላይ ብቻ ይሆናል። ሙሉውን የዚህ መጣጥፍ መነሻ የሆነውን የመ/ር ምህረተአብን የዲቪዲ ስርጭት ለማየት http://www.youtube.com/watch?v=Y47C_SCkjIA ላይ ማግኘት ይቻላል።

አንደኛው ነጥብ ርእሱ ሲሆን ሁለተኛው ይኸው ሰባኪ በተለይ አንዱና ዋናው ነጥቡ ስለሆነው ስለ ማርያም በሰፊው ከሰበከው ከ2ኛው ዲቪዲ የተወሰደ አሳብ ላይ ሆኖ ስብከቱን ከስነ አፈታት አንጻር መመልከት ነው። በተመሳሳይ ርእስ የተዘጋጀው ሁለተኛ ዲቪዲም በመረጃው መረብ በhttp://www.youtube.com/watch?v=GPBzlS5Le_A&feature=related ይገኛል።

የቪድዮ መልእክቱን ከተመለከትኩ በኋላ መልእክቱን ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ለማየትና ለመገምገም ፈለግሁ። በዚህ መጣጥፍ ላደርግ የሞከርኩት ይህን ነው። ግን በዚህ ላበቃ አልፈልግም በኦርቶዶክሳዊ ነገረ ማርያም (Mariology) ዋነኛ አገራዊ ምንጭ ተደርጎ የሚታየው ተአምረ ማርያምን በተመለከተም ጥቂት መባል ያለበት መስሎ ተሰማኝ። አሁን አሁን ነገረ ማርያሙ ወደ አምልኮተ ማርያም (Mariolatry) የተለወጠ ሆኖአል። ይህንን ከመካከለኛው ወይም መደዴው ምዕመን ጋር ስለ ማርያም በመነጋገር መረዳት ይቻላል።

## እውን ጅሃድ ታወጀ?

ርእሱ *ፕሮቴስታንታዊ ጅሃድ በኢትዮ/ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን ላይ ሲፋፋም* ይላል። በተመሳሳይ ርእስ ሌላ መጽሐፍም ተጽፎ ተሰራጭቶአል።[1] በርእሱ ላይ እንግሊዝኛውም (ፕሮቴስታንታዊ) ዐረብኛውም (ጅሃድ) አልቀረም። ጅሃድ የሚለው ቃልም በግርድፉ ተተርጉሞ የክተት ሠራዊት ዘመቻ ተደርጎ ቀርቦአል። ርእሱ ለአንድ የወንጌላዊ እምነት ሰባኪ የተሰጠ ምላሽ ሳይሆን በጠቅላላው ወንጌላውያን አማኞች አመለካከት ላይ የቀረበ ርችትም ይመስላል። ስሕተቱ እዚህ ላይ ነው።

የንግግርና የጽሑፍ ወይም የኅሊና ነፃነት በሚፈቀድበት ኅብረተ ሰብ ወይም መንግሥት ውስጥ ማንም ሰው ምንም ቢናገር በቤተ ክርስቲያን ወይም በአንድ ሃይማኖት ላይ ጅሃድ ታወጀ ማለት ስሕተትም፥ ሐሰትም፥ ነውርም፥ ወንጀልም፥ ኃጢአትም ነው። መጋቢ ዳዊት ሞላልኝ የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሲሆን በቤተ ክርስቲያኒቱ መጽሐፍ ቅዱስን ቢያስተምር ተልእኮው፥ ጥሪው፥ ኃላፊነቱ ነው። የካ ሚካኤል ወይም ዲማ ጊዮርጊስ ቅጽር ውስጥ አንድ ዲያቆን ወይ ቄስ ወይም ባህታዊ፥ ‘እነዚህ ብሮቴስታንትዎች የጌታን እናት ትተው ልጇን ይሰብካሉና የእግዝእትነ ጠላቶች ናቸው፤ የእርሷ ጠላቶች የኛ ጠላቶች ናቸው’ ብሎ ሰበከ እንበልና ይህን ስላለ ኦርቶዶክሳዊ ጅሃድ ታወጀብን ብንል አልተሳሳትንም? ተሳስተናል። ነጠላ ስም ጠርተን ‘ዲያቆን ወይም መምህር እገሌ በስብከቱ በዚህ ርእስ ላይ እንዲህና እንዲህ አለ፤ ይህ አባባል ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ሲፈተሽ . . . ’ ከማለት ያለፈ ውርጅብኝ የተገባ አይደለም።

የመጋቢ ዳዊትን ስብከት ያየሁት ከዚሁ ዲቪዲ ቅንጣቢውን ብቻ ነውና ብዙም መተቸት አልችልም። ካየሁት ግን የመጋቢ ዳዊት አቀራረቡ የራሱ ስልት ቢሆንም ስለተነሱት ነጥቦች የነጠሩ የቃሉን ጥቅሶች በግልጥ፥ በተሻለና በጨዋ ቋንቋ፥ ማስረጃዎችን በግልጽና ምንጮችን በመጥቀስ ማቅረብ ይችል ነበር እላለሁ። በሙሉው ስላላየሁት አላቀረበም ወይም በደፈናው ሳያቀርብ ቀረ ማለትም አልችልም። ይሁን እንጂ የስሕተቶች አስረጂያችን አባባል፥ ወይም የስሕተቶች ማረጋገጫችንና መልስ መቅጃችን የኢንተርኔት ካፌ፥ ወይም እውቅ ሰባኪ፥ ወይም ሌላ መሆን የለበትም። ይህ ፓስተር ዳዊትን ይመለከታል። በመ/ር ምህረተአብ የተወሰደው የቪድዮው ክፍል ግን ቅንጣቢ ብቻ ሆኖ ለማናደድና በጥላቻ ለማነሣሳት እየተቆረጠ የተለጠፈ ነው። እንደተነገረው በሕግ ዳኝነት ፊት መቆም አንድ ነገር ነው፤ ግን ሰፊውን ኦርቶዶክሳዊ ምእመናን ጅሃድ ታወጀባችሁ በማለት ለምላሽ ማነሣሳት የራቀ ግብ ያለው ይመስላል። ይህን ያልኩት ምላሹ የታቀደው መልስ ለመስጠት ብቻ ሳይሆን ስነ ልቡናዊ የጥላቻና የብቀላ ቅስቀሳ ለመጫር ስለሚመስል ነው።

ነባራዊውን እውነት መናገርና ከቃሉ አንጻር ስሕተትን መግለጥ ግን ወንጀልና የጦርነት ክተት አዋጅ ወይም የዲቪዲ ዝግጅቱ እንዳለው ጅሐድ አይደለም። ሙስሊሞች ነቢያችን ተዋረደ፥ መልኩ በወረቀት ላይ

[1] በእሱባለው በለጠ የተጻፈው *የገሃነም ደጆች ፕሮቴስታንታዊ ጅሀድ በኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶነት ላይ ሲፋፋም* የሚል መጽሐፍም በርእስ ተጋሪ መጽሐፍ ነው።

ተሳለ፥ መጽሐፋችን ላይ ተጻፈበት፥ ስለ ኢሳ (ኢየሱስ) አዳኝነት በጆሮአችን ተነገረን፥ ወዘተ፥ ብለው የክርስቲያኖችን አፍ ለመዝጋት ብቻ ሳይሆን ነፍስ ለማጥፋት በየቦታው እንዳደረጉት ያለ ዘመቻ ማወጅና ማዝመት ውጤቱ ከፉ ነው። ጅሃድ እንደምናውቀውና እንደምናየው ለሃይማኖት ቀንቶ ሥጋን መግደል ነው። በእውነቱ የትኛውም ሃይማኖት በታሪክ ውስጥም ሆነ በዘመናችን ነፍስን በማጥፋትና በማስጠፋት የሚደሰትና የሚኮራ ከሆነ፥ የሚያደፋፍርና የሚያበረታታም ከሆነ ሃይማኖት ሳይሆን ፖለቲካ ነው። ያውም ጥሬና አስቀያሚ ፖለቲካ!

አንድ ወንጌላዊ ሰባኪ ያመነበትን ነገር መስበኩን ጅሃድ ካሉት በወንጌላውያን አማኞች ላይ የደረሱትን አካላዊና ቁሳዊውንም የጨመረ ስነ ልቡናዊና መንፈሳዊ ስደትን፥ አካላዊ ጉዳትንና የንብረት ውድመትን ምን ብለው ሊጠሩት ነው? በጨዋነት መነጋገርና መከራከር ብቻ ሳይሆን በጨዋነት መነታረክም እንኳ እኮ ይቻላል። መ/ር ምህረተአብ የዳዊትን ስብከት ጅሐድ ብሎ ከሰየመው በቀጣዩ ጅሃድ ብሎ በሰየመው ነገር ላይ የጅሐድ ምላሽ ጦር ቢያስከትትስ? አስከትቶም ሰባኪውን ወይም ማኅበረ ምእመናኑን ወይም ሰፊውን ወንጌላውያን አማኞች ለማሳደድ ቢጋበዝስ? ቅንብሩና አሰያየሙ ይህን ለማድረግ የማይመለስ ወይም ወደዚያ አቅጣጫ የሚያዘግም ያስመስለዋል። ቃል ተነግሮብናል፤ ስብከት ተሰብኮብናል እና ሰይፍ መዝዘን እንነሣ ማለቱ ነው? በዲቪዲው መግቢያ የተጠቀሰው ቁጣ መቀስቀስ አዝማሚያው ምንድርነው? የቪዲዮ ዝግጅቱ እንደተናገረው ከላይም እንደጠቀስኩት ጉዳዩን ወደ ሕግ አቅርቦ፥ 'እንዲህ ሰበከ' ብሎ መክሰስ ወይም መጠየቅ አንድ ነገር ነው። ሕግ እስካስኬደው ድረስ። ጅሃድ አወጀብን ብሎ መክሰስ ግን ይቻል ይሆን? ስለ እርሱና ርእሱ ስሕተት ይህን ካልኩ ላብቃና ወደ አንዱ የመ/ር ምህረተአብ ስብከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ ላምራ።

## ነገረ - ማርያም በመደደው ምእመን ዘንድ

ሁለተኛው ነጥብ በዚሁ የመጋቢ ዳዊትን ስብከት ጅሃድ ባሰኘው ሰባኪ በመ/ር ምህረተአብ የተሰበከው ክፍል ስለ ጌታችን እናት ስለ ማርያም የተነገረው ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ መደገፊያ መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎና ተጠናቅቆ ካበቃ ከሙቶና ከሺህ ዓመታት በኋላ የተደረሱና የፈሉ መልከአ እገሌ፥ ድርሳነ እገሌ፥ ተአምረ እገሌ፥ ውዳሴ እገሌ ወዘተ የተባሉ ድርሰቶች መሆንም የለባቸውም። ለነገሩ መጽሐፍ ቅዱስን በድርሳናቶ ለመደገፍ መሞከር ምሰሶን በሰንበሌጥ እንደመደገፍ ነው። መለኮታዊ ምንጭነት ያለውና በክርስትና ትምህርትና አኗኗር ላይ ከምንም ሕግ በላይ ሥልጣን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ በመሆኑ መተኮር ያለበት ይህ ቃል ነው። በዚህ መጣጥፍም የምሞግተው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ማርያም ይህን ይላል ወይስ አይልም? ደግሞም የሚለው ምንድር ነው? በማለት ነው።

የአማካዩ ኦርቶዶክሳዊ ምእመን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀት ከቁጥር የሚገባ አይደለም። ደግሞም ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ የሚያውቀው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ቢጋጭም ቢጣላም ከዚያ ውጪ ያለውን ነው። ልጅ ሳለሁ ስለ ማርያም የማውቀው ነገር መልአክተን ካስተማሩኝ የኔታ፥ የክርስትና አባቴ ከሆኑት መሪጌታ፥ እንዲሁም ከእናቴ የሰማሁት ነው። በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ የሚበረታታ ልማድ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ስጀምር ስለማርያም እሰማ የነበረው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሌለ ብቻ ሳይሆን ፈጽሞ የሚጣላና የሚጋጭ ነገር ሆኖ አገኘሁት። እንግዲህ ይህ የአማካዩ ምእመን ብቻ ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎቹና ሊቃውንቱም ትምህርት ሆኖ ሲገኝ ግጭቱን እንዴት ሊያስታርቁ እንደሚሞክሩ ማየት ራሱ ትንግርት ነው። ባለ ሥልጣኑ መጽሐፍ ተለይቶ አልተቀመጠም፤ ወይም ሁሉም መጽሐፍ እኩል ሥልጣን አለውና መታረቅ አይችሉም።

በዚህ የፈረንጆች ገና ዕለት በአንድ ቤት ለራት ታድመን ነበር። ከእራት በፊት ቃል እንዳካፍል ተጠይቄ ነበርና ገላ. 4፥4ን አካፈልኩ። ከእራት በኋላ በጭውውት ጊዜ አንድ ሰው፥ "ቅድም ያካፈልከው ቃል ጥሩ ነው፣ ግን ለምን ሴት አልካት" አለኝ። ማርያምን ማለቱ ነው። "ወንድ ስላልሆነች ነዋ!" ብዬ ልመልስ ቃጥቶኝ ነበር። አሳቡ ገብቶኛል። ሊጠይቅ የፈለገው፥ 'ለምን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አላልከም፥ ሴት ስትል እኮ እርሷን ማዋረድህ ነው፤ ማቃለልህ ነው' ለማለት ነው። ከሌላ ወንድም ጋር ተረዳድተን ቃሉ ሴት እንደሚልና ሊል የፈለገበትን ዓላማም አስረዳን። ሰውየው አሁንም፥ "ቃሉ እንደዚያ ካለ ተሳስቷል፤ ተርጓሚዎች አሳስተው ጽፈውት ነው" አለን። አሁንም አለመሆኑን አስረዳነው። እርሱ ራሱ አነበዋለሁ ባለው የግዕዝ አዲስ ኪዳንም ሆነ በሌሎች ትርጉሞችም ቋንቋዎች ቃሉ ያው መሆኑን ነገርነው። ይህን አስረድተን እንዲያውም ጌታ ኢየሱስ ራሱ አገልግሎቱን በጀመረና ውኃውን ወደ ወይን በለወጠ ጊዜ፥ እንዲሁም ሁሉን ጨርሶ በመስቀል ላይ ሳለ እናቱን ማርያምን፥ "አንቺ ሴት . . ." እንዳላት (ዮሐ. 2 እና 19) ነገርኩት። ይህ ደግሞ ማሳነስ ወይም ማቃለል ሳይሆን የተለመደ አባባልም፥ የግንኙነትን ድንበር የሚገድብም አገላለጽ ነው አልኩት። ይህንን ስል፥ "ኢየሱስ ይህንን ብሎ ከሆነ [ማርያምን አንቺ ሴት ብሎ ከሆነ] እርሱ ራሱም፥ ልክ አይደለም፥ እናቱን እንዴት፥ 'አንቺ ሴት' ይላል? ይህን ብሎ ከሆነ እርሱም ተሳስቷል" አለን። ለማርያም የሚሰጠው የተሳሳተ ምልከታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንኳ ተሳስቶአል ከማለት የማያግድ ነው። ይገርማል! ያሳዝናልም!

ይህ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ከቶም አንብቦ አያውቅምና ኢየሱስ ያለውንና ያላለውን ብቻ ሳይሆን ኢየሱስን ራሱን የሚያውቀውም በስማ በለው ነው። ክርስቲያን ነኝ የሚል ሰው ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ያለምንም መጠራጠር መቀበል ይገባዋል። ሌሎች መጻሕፍትንና ድርሰቶችን ከሚያነብበው በላይም መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይጠበቅበታል። መጻሕፍትን ወይም ድርሳናትን፥ ገድላትን ወይም መልክአዎችን ከተጻፉባቸው ታሪካዊ መቸት አንጻር ማየትና መተቸትም መበረታታት አለበት። እውነት ከሆነ ይበልጥ ይገለጠዋል፤ ውሸትም ከሆነ ይገለጠዋል። ውሸት ካልሆነ በቀር ትችትን ወይም ሒያሴን የሚፈራ መጽሐፍ መኖር የለበትም።

በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ማርያም የተሰጣት ስፍራ ለመረዳት የሚከብድ መለኮታዊ ሥልጣን ነው። ልክ በስዕሎቻቸው ሁሉ ትንሽ ኢየሱስና ትልቅ ማርያም እንደምትታየው ሁሉ ለማርያምና ለኢየሱስ የሚሰጡት ስፍራም በዚያ ልክ የተመጠነ ይመስላል። በአማካዩ ኦርቶዶክሳዊ ምእመን ምናብ ውስጥ የተሳለው ኢየሱስ እናቱ ማርያም የምትጠይቀውን ወይም የምትነግረውን ሁሉ ተቻኩሎ የሚፈጽም፥ አንዱንም እንቢ የማይል ታዛዥ ልጅ ምስል ነው። በኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖት የኖርን ሁሉ ይህን እናውቃለን። ለአንዳንዶች ልክ እንደ ስዕሉ ኢየሱስ አሁንም ምራትና ድጋፍ፥ ጥበቃና ክብካቤ የሚያሻው ሕጻን ይመስላቸዋል።

ወንጌላውያን አማኞች ማርያምን እንደሚያጣጥሉ የሰበኩ አንድ ቄስ፥ "እነዚህ መጤ የፈረንጅ ሃይማኖት ሰባኪዎች እናቱን ጥለው ልጁን ይሰብካሉ። ይህ ማለት ከታሸገ የምግብ ቆርቆሮ ውስጥ ምግቡን በልቶ ቆርቆሮውን ወዲያ መጣል ነው እኮ!" እንዳሉ አንድ የሰማቸው ጓደኛዬ አጫውቶኝ ነበር። የቄሱ ምሳሌ በመጀመሪያ ደካማ ብቻ ሳይሆን

ትክክለኛ ያልሆነ ምሳሌ ነው። ማርያምና ኢየሱስ ቆርቆሮና ሥጋ አይደሉም። ሁለተኛም፥ እንዲያው ሆኑ ቢባልስ፥ ከቆርቆሮው ሥጋውን የበላ ሰው ቆርቆሮውንም መቆርጠም አለበት የሚባል ግዳጅ ውስጥ ቢገባ ስሕተት አይሆንም? ወይም ሥጋውን የበላሁበት ቆርቆሮ ነውና ብሎ ለቆርቆሮው ማማ ሠርቶ ሊያጥንለት ወይም ሊሰግድለት ተገቢው ነው? አይደለም።

ስለማርያም ከኦርቶዶክሶች ጋር መነጋገር የሚያጣላ ተደርጎ ስለሚነገር ብዙዎች አያነሱትም። ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን የሚቀበሉ ሁሉ የተጻፈውን ቃሉን በአክብሮት ሊቀበሉ ግድ ነውና የሚያጣላ ወይም የሚያስቀይም ወይም ሌላ ተብሎ ዝም አይባልም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተጻፈውን እንደተጻፈ ያህል ተደርጎና ተቆጥሮ ሰዎች ያለ ጥያቄ እንዲቀበሉት ወይም የተጻፈውን እንዳልተጻፈ ሁሉ እንዲዘልሉት ወይም ዐውደ ወጥ አፈታት እየተፈታ ያላለውን እንዲል እንዲደረግ የተገባ አይደለም።

መጽሐፍ ቅዱስ በተናገረባቸው ቦታዎችና ጉዳዮች ሁሉ የተናገረውን እንደምናከብር ሁሉ ዝም ባለባቸው ቦታዎችና ጉዳዮችም ዝምታውን ማክበር አለብን እንጂ ያንን ዝምታ በራሳችንና ሰዎች በፈጠሩት ምናባዊ ትረካ መሙላት የለብንም። ለምሳሌ፥ ወንጌላት በአራት የተለያዩ ሰዎች የተጻፉ የጌታ ታሪኮች ናቸው። ከአራቱም ውስጥ በሁለቱ ወይም በሦስቱ ወይም በአራቱም ውስጥ የተደጋገሙ ጉልህ ታሪኮች አሉ። በአንጻሩ ደግሞ በአንዱ ብቻ የተጻፉ አሉ። ጨርሶውኑ ያልተጻፉም አሉ። ጌታ በአሥራ ሁለት በመቅደስ ከተገኘበት በቀር በሠላሳ ዓመቱ አገልግሎት እስኪጀምር ያለው ታሪኩ ፈጽሞ አልተጻፈም። ታዲያ ይህን 'ጎዶሎ' ለመሙላት ታሪክ መበጀትና መፈጠር አለበት? አስፈላጊ ቢሆን ኖሮ ከመወለዱ በፊት የሆነውን ታሪክ ከማርያም የሰሙት ማቴዎስና ሉቃስ አይጽፉልንም ነበር? ግን አልተጻፈልንም። ለምን? ይህ ለመዳናችን አስፈላጊያችን አይደለም? ደግሞም እንዲጽፉ የመራቸው መንፈስ ቅዱስ ይህ እንዲገባ አላደረገም። ቃሉ ዝም ሲል ዝምታውም የመናገሩን ያህል አክብሮት ይገባዋል።

ስለ ማርያም የተጻፈልንም እንዲሁ ልናውቀው የተገባንን ያህል ነው። ሌላ ማወቅ ያለብን ወይም የሚያስፈልገን፥ ለትምህርትና ለተግሳጽ፥ ልብን ለማቅናት በጽድቅ ላለው ምክር የሚጠቅመን ቢሆን በተጻፈልን ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ የፈለግነውን ቁጥር ጽፈንበት ወደ ገንዘብ የምንለውጠው ባዶ ቼክ አይደለም፤ ባልተጻፈበት ሰነድ ሰዎች ያሻቸውንና የፈጠሩትን ሊዶሉ አይገባም። እነዚህ ስለ ማርያም የተጻፉ የኋላ ዘመናት ታሪኮች የእግዚአብሔር መንፈስ ያልመራቸው የሰዎች ፈጠራዎች እና ተረቶች መሆናቸውን የምናውቀው ከተገለጠውና ከተጻፈው ቃሉ ጋር የተጋጩ ሲሆኑ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ካልመራቸው ደግሞ ሌላኛው መንፈስ እየመራቸው ነው ማለት ነው። ድርሳናት ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ከማቅረብ ከክርስቶስ የሚያርቁ ሲሆኑ፥ ክርስቶስን ኃይለኛ ዳኛ፥ ጨካኝ ጌታ አድርጎ ስሎ ድርሳኑ የተጻፈለትን ሰው ወይም ሴት ርኅሩኅ፥ አዛኝ፥ ይቅርታን ከየትም ገብቶ የሚያመጣ ሲደረግ ይህ በኃጢአተኛ ሰውና በኃጢአት መድኃኒት መካከል ጣልቃ መግባትና መሸፈን ነው።

መልክአ ማርያም፥ ተአምረ ማርያም፥ እና ውዳሴ ማርያም የተባሉት መጻሕፍት ውስጥ የተጻፉት ትረካዎችና ልብ ወለዶች ከወንጌሉ እውነት ጋር የሚጋጩ ብቻ ሳይሆኑ አምልኮን ከእግዚአብሔር የሚቀንሱና ለሌላ የሚያሳልፉ፥ እምነትንም በአንዱ አዳኝ ላይ ከማድረግ የሚያስጥሉ ናቸው። መዳን በክርስቶስ በኩል ፈጽሞ የቀረበ ነውና የሚያምን ሁሉ በነጻ የሚቀበለው ነው። ለኛ ነጻ ነው ማለት ግን የተከፈለ ዋጋ አልነበረም ማለት አይደለም። ጸጋው ነው መዳንን ነጻ ያደረገው።

ማርያምን በተመለከተ የተፈጠሩና በታሪክ ውስጥ እያደጉ የመጡ ትምህርቶች አሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈው ታሪኳ በጣም ውብ ታሪክ ነው። ለጌታችን ሥጋ መልበስ የእግዚአብሔር መሳሪያ ሆናለች። መልአኩ ገብርኤል ተልኮ ከተናገራትና ኢየሱስን ከመጸነሷ ጀምሮ (እውነተኛው ታሪኳ እዚያ ነው የሚጀምረው) እስከ መስቀሉና ከእርገቱ በኋላም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብራ መገኘቷ በግልጽ ተጽፎ ይገኛል። በኋላ ግን በካቶሊክ እና ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ከመወለዷ በፊት ያለው ታሪኳ፥ ያለኃጢአት ከመጸነሷ ጀምሮ ወደ ሰማይ እስከማረጓና የአሁን የአማላጅነትና የቤዛነት ሥራዋ በሰፊው ይተረካል። ይህ በ2ጴጥ. 1፥16 በብልሃት የተፈጠረ ተረት ነው። በ2ጢሞ 4፥4 *እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፥ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ* የተባለውም ይህ ነው።

በኦርቶዶክሳዊ ወካቶሊካዊ አስተምህሮ ስለማርያም ከተፈጠሩት ተረቶች ዋናዎቹን በመጠኑ በዝርዝር ብንመለከታቸውም አንኳሮቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. ያለኃጢአት መጸነሷ። (ጠበቅ የሚደረገው ፊደል ጸ ነው) ይህ ኢየሱስን ያለኃጢአት መጸነሷን ሳይሆን ራሷ ያለ አዳም ኃጢአት ተረግዛ መወለዷ ነው። ልክ ኢየሱስ በተወለደበት መልኩ ነው የተወለደችው ሊሰኝ ነው፡፤ ይህ ወላጆቿን ከአዳም ዘር ውጪ ያደርጋቸዋል። ይህ ኢየሱስን ከአዳም ዘር የውርስ ኃጢአት ነጻ አድርጎ ለማቅረብ በወላጆቿ ላይ የተፈጸመው መለኮታዊ ተአምር መሆኑ ነው። ማርያም ያለኃጢአት መጸነስና መወለድ ከቻለች ኢየሱስ እንዴት ያለኃጢአት ሊወለድ አይችልም? ይህ ኢየሱስን ከውርስ ኃጢአት የጸዳ አድርጎ ለማቅረብ የተደረገ ሙከራ ብቻ ሳይሆን በአቋራጭ ለማርያም ልዩ ፍጡርነትን ለማቀዳጀት የተደረሰ ፈጠራ ነው። በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ይህ ትምህርት የተደነገገው እንደ ኤሮጳውያን ቆጠራ በ1854 ነው። በእኛዎቹ መቼ መጣ ይህ ድንጋጌ ቢባል የኖረ መሆኑ ብቻ ይነገራል። ኃጢአት የሌለበት አዳኝ እንደማያስፈልገው የታወቀ ነው። አዳኝ የማያስፈልጋት ቢሆን ኖሮ ማርያም በሉቃ. 1፥47 እንደተጻፈው በመድኃኒቷ ሐሴት ስለምን አደረገች?

በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ በተጻፈው በኢየሱስ የትውልድ ሐረግ ውስጥ ከማርያም ጋር አራት ሴቶች ተጠቅሰዋል። በመጀመሪያዎቹ 6 ጥቅሶች ስማቸው የተጻፈልን እነዚህን ሴቶችና ታሪካቸውን ስንመረምር የሚያስመሰግንና የሚያስወድስ ታሪክ ያላቸው ሴቶች ከቶም አይደሉም። ትዕማር ማለት ይሁዳ ከልጁ ሚስት መንታ ልጆች የወለደባት ናት። ራኬብ የተባለችው ሴት በብዙ ትርጉሞች ረዓብ ተሰኝታለች፤ ከሆነች የኢያሪኮዋ ጋለሞታ መሆኗ ነውና ከጠፉት አሞራውያን ወገን ናት። ሩትም ፈጽሞ አይሁዳዊት አይደለችም፤ ሞዓባዊት ናት፤ በሐረጉ ውስጥ ግን ገባች። ቤርሳቤህ እንዲያውም የዳዊት ሚስት ሳትሆን የኦርዮ ሚስት ነው የተባለችው፤ ታሪኩ መጥፎ ነው። የነዚህ አሳፋሪ ሴቶች ታሪክ ከንጉሡ ኢየሱስ ታሪክ ውስጥ ተቀርፈው አልወጡም። ማርያም ልዩ ፍጡር ኖራ ቢሆን ከነዚህ ለማነጻጸር እንኳ የማን ልጅ መሆኗ አይጻፍም ነበር። የትውልድ ሐረግ የወንድ ብቻ ሳይሆን እናቶችም የሚጻፉበት መሆኑ ከብሉይ ኪዳን ነገሥታት ይታያል። በተአምረ ማርያምና በሌሎቹም መልካ መልኮች የተጻፉት የማርያም መወለድ ከኢየሱስ ያልተናነሰ ትንግርት ነውና ይህ በእውነት ብዙ መቶዎችና ሺህዎች ዓመታት ቆይቶ መጻፍ ነበረበት? እውነት ኖሮ ቢሆን ከወንጌሉም በፊት መጻፍ ነበረበት።

2. ዘላለማዊ ድንግልና። ኢየሱስ ከድንግል መወለዱ በግልጽ ተጽፎአል፤ ማቴ. 1 እና ሉቃ. 1። ዮሴፍም ማርያምን የበኩር ልጅዋን እስከትወልድ ድረስ እንዳላወቃትም በግልጽ ተጽፎአል። ስለዚህ የጌታ ሥጋ መልበስ ልደት ፍጹም ልዩ ነው። ሥጋ በመልበሱም ፍጹሙ አምላክ ፍጹም ሰው ሆኖአል። ታዲያ ማርያም ጌታን ከወለደች በኋላ ሌላ ከወለደች የጌታ ማንነት እንዳይለወጥ ነው? ጌታማ ከድንግል ሥጋን ነስቶአልና ከዚያ በኋላ ማርያም ብትወልድም ባትወልድም የእርሱ ማንነት አይለወጥም። የእርሷ ግን አሁን እንደተሰጣት ያለውን አይሆንም። ስለዚህ ለእርሷ የተለየ ስፍራ ለመስጠት ነው ከመውለዷ በፊት ድንግል፥ ስትወልድ ድንግል፥ ከወለደችም በኋላ ድንግል ሆና የኖረች የተደረገው።

ማርያም ኢየሱስን ከመውለዷ በፊት ብቻ ሳይሆን ጊዜ ወሊድም ድንግል መደረጓ የኢየሱስን መወለድ ለማርያም ሲባል፥ ፍጹም የሆነ አካሏ ከስቃይ ነጻ እንዲሆን ሲባል ጭንቅ የሌለበት ሆኖአል። ይህን ለመረዳትም ለማስረዳትም የሚከብድ ብቻ ሳይሆን ማርይምን ከሴቶች የተለየች የሚያደርግ ትምህርት ነው። መልአኩ ለማርያም የተናገራት አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ ነው እንጂ ከሴቶች የተለየሽ አይደለም። ይህ የማርያምን ሴትነት ብቻ ሳይሆን የኢየሱስን ሰውነትም የሚያጠያይቅ የሚያደርግ ትምህርት ነው። ማርያም ስትወልድም ድንግል ከሆነች እርሷ ከምጥ ጭንቅ ትድን ዘንድ ኢየሱስ እንደ ሰው ሳይሆን እንደ ሌላ ፍጡር ሆኖ ነው የተወለደው ማለት ነው። አዲስ ክርስቲያን ሳለሁ መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት ካስተማሩኝ አንዱ ቀድሞ ቄስ የነበሩ መምህር ይህን ኢየሱስ ሲወለድ እርሷ ድንግል ሆና እንድትቀር እርሱ ልክ እንደ ቅቤ ለስላሳ ሆኖ ከውስጧ እንደወጣ ያስተምሩ እንደነበሩ አስተምረውን ነበር። ይህ ሰውነቱን አይጋፋም?

3. ወደ መንግሥተ ሰማያት ማረጓ። በካቶሊክ አስተምህሮ የምድር ኑሮዋ ዘመን ሲፈጸም ሳትሞት እንደ ሔኖክ ወደ ሰማይ ማረጓ ነው የተጻፈው። በኦርቶዶክስ ደግሞ በ64 ዓመቷ ሞታ ተቀብራ በ3ኛው ቀን ተነሥታ ማረጓ ተጽፎአል። የቱ ትክክል ሊሆን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ በሐዋ. 1፥14 ከጌታ ወንድሞች ጋር ስለ ማርያም ከተናገረ በኋላ ስለ እርሷ ምንም የተናገረው ነገር የለም። ታዲያ ስለማርያም ዕርገት መጻፍ ያስፈለገው ማንን የተለየ ለማድረግ ነው? በግልጽ እንደተጻፈልን የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው፤ ስለዚህ ማርያም ያለኃጢአት በመሆኗ መሞት የለባትምና ለምን አለመሞቷ አይጻፍ? ካቶሊኮቹ ይህን ለማስተካከል ይሆናል አለመሞቷን የጻፉት። ይህን ትምህርት ደንግገው ያቆሙትም በሺህ950 ነው። መቶ ዓመት እንኳ ያልደፈነው አዲስ አስተምህሮ ነው። በኦርቶዶክስም ሞቷ ከተጻፈ አይቀር ከሙታን ተነሥታ ማረግ ኖረባት። ያውም በ3ኛ ቀን!

4. አማላጅነትና ቤዛነት። ያለ ኃጢአት የተጸነሰችው፥ ለዘላለሙ ድንግል የሆነችው፥ ወደ ሰማይ ያረገችው ማርያም ሥራዋ በዚያ ብቻ ማብቃት የለበትም። ይህኛው ደግሞ አሁንም አማላጅ ሆና የፈለገችው፥ የለመነችው፥ የጠየቀችው ሁሉ እየተፈጸመላት የምትኖር የመሆኗ ትምህርት ነው። የመንግሥተ ሰማይ ደጅ ተሰኝታ በእርስው በኩል ካልሆነ ማንም ወደ እግዚአብሔር የማይደርስ ተደርጎ ያስተምሯል። ኢየሱስ ዳኛና ፈራጅ እርሷ መሐሪና ርኅሩኅ ተደርጋ ተስላለች። እንዲያውም ቤዛ ናት፤ የዳንነው በእርሷ ደም መሆኑም ተጽፎአል። በመስቀል ላይ የፈሰሰው የጌታ ደም የእናቱ ደም ነውና ያዳነን የማርያም ደም መሆኑ በግልጽ ተነግሮአል።

(5. መገለጧ።) ይህ በካቶሊክኛ አካሄድ ከሄድን ሌላ አምስተኛ ሆኖ መጠቀስ የሚችል ነጥብ ነው። ያም የማርያም በታሪክ ውስጥ በራእይም በአካልም እየተገለጠች ለሰዎች መታየት ነው። በተለያዩ አህጉራት ይህ በመከሰቱ ካቶሊኮች በተገለጠችባቸው ቦታዎች ገዳማት በመገደምና ሕንጻዎች በማነጽ መታሰቢያዋን እያበዙት ነው። የተገለጠችባቸው ቦታና ጊዜዎች ከሺህ አልፈዋል። የሚያሳፍረው ተገልጣ ተናገረች የሚባለው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ቢቃረንም እንኳ እንዲያው መቀበሉ ነው። በኦርቶዶክስ በተአምረ ማርያም ከተጻፉት ሌላ በአካል ተገለጠች የተባለባቸው ሕዝባዊ ታሪኮች ከቁጥርም አይገቡም። በ1990ዎቹ አጋማሽ አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ታየች እየተባለ የተወራና የተሠራ ነገር ነበረ። በቅርቡ ደግሞ ‘ማርያም ተገለጠች’ ሳይሆን ‘ማርያም ነኝ’ የምትል ሴትም ተነስታ ሽብር መፈጠሩ ተደምጦአል።

እነዚህ ነገሮች ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነትና ትምህርት ጋር ይጋጩ ወይም ይስማሙ ግድ ሳይኖር ነው በድፍኑ ቃሉን የማይመረምርና የማይጠይቅ ሕዝብ አፍንጫው ተይዞ የሚጋተው። ጥቂት ጥያቄዎች ቢጠየቁ ተገቢ ነው። እነዚህን ጽሑፎች ማን ጻፋቸው? ለምን ጻፋቸው? መቼ ተጻፉ? ቀድሞ ከተጻፉ ትምህርቶች በምን ይስማማሉ በምንስ ይለያሉ? ከመጽሐፍ ቅዱስ ንጹሕ ትምህርት ጋርስ ይስማማሉ ወይስ ይጋጫሉ? በተለይ የመጨረሻው ጥያቄ አንገብጋቢ ነው። ሰውን ወደ አምላክነት ስፍራ ከፍ ቅድርጎ የሚሰቅል፥ የአምላክ የእግዚአብሔርን ሥልጣን ከፍሎና ገምሶ የሚወስድና የሚቀንስ፥ ከእውነት ቃል ጋር የሚጋጭ ማናቸውም ድርሳን፥ ገድል፥ ተዓምርና መልክ ምንጩ ሰይጣን እንጂ መንፈስ ቅዱስ አይደለም።

## ከውን ማርያም ከግዝከት ናት?

እርግጥ ነው ማርያም የጌታችን እናት ናት፤ ጸጋ የሞላባት ናት፤ ከሴቶች ሁሉ የተለየች ናት፤ የማኅጸንዋ ፍሬ የተባረከ ብጽዕት ናት። ግን እመቤት (እግዝእት) ናት? አይደለችም። እግዝእት ማለት አንስታዊ የጌታ ወይም የእግዚአብሔር ማዕረግ ነው። ከጌታ በቀር ደግሞ ጌታ የለም። ይህ ስግደትንና አምልኮን ከጌታ በቀር ለሌላ ለመስጠት የሚደረግ ቀጥተኛም ይሁን ተዘዋዋሪ እርምጃ ከዓሠርቱ ትእዛዛት በቀጥታ ሁለተኛውን ትእዛዝ የሚጥስ ነው። ምስልም መሥራት ስግደትም ማቅረብና ማምለክ ይህ እንጂ ሌላ ከቶም አይደለም።

ስለ ማርያም የተጻፉት ድርሳናትና ገድላት በካቶሊካውያንም ሆነ በኦርቶዶክሳውያን የተጻፉባቸውንና የተደረሱባቸውን ዘመናት ብንመረምር ከታሪኩ ዘመን በእጅጉ የራቁና የኋላ ምዕት ዓመታት ድርሳናት ሆነው እናገኛቸዋለን። ለምሳሌ፥ ስለማርያም ዕርገት የተጻፉ ድርሳናት ከ6ኛው መቶ በፊት አልነበሩም። በካቶሊካውያን ዘንድ በ13ኛው መቶ ከፊል ተቀባይነት እየተቀዳጀ መጥቶ ርእሱ ክርክር ሲደረግበት ኖሮ በካቶሊካዊ ሃይማኖት ዶግማ የሆነው በ1950 ነው። የማርያም ያለኃጢአት መጸነስ በክርክር ኖሮ በ1854 ነው ይፋ ዶግማ የሆነው። በኛ አገር የገነነ አምልኮተ ማርያም የደራው በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ይመስላል። ካቶሊካዊ ግንኙነትም ተጀምሮ ነበርና ይህ አጉልቶት ይሆን? በዘመኑ ሊጎበኝ በመጣው ፈረንሳዊ ሰው እና በአባ ጊዮርጊስ መካከል ንግግር ተደርጎ ነበረ። ከዚያ በኋላ የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ወደ ቫቲካን ተላከ። የሮማ ቤተ ክርስቲያን ቸል ብትለውም ግንኙነቱ ለፖርቱጋሎች መምጣት ምክንያት ሆኖ ነበር። ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ራሱ የማርያም አምልኮን በአዋጅ ሕጋዊ ያደረገ ለመስቀልና ለስዕል የማይሰግዱ በጽኑዕ እንዲቀጡ ያደረገ ንጉሥ ነው። ተአምረ ማርያም የተተረጎመውም በዚህ ዘመን መሆኑ ይገመታል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ተደንግጎ ሲያበቃና ወንጌላቱ አራቱ ብቻ መሆናቸው ሲረጋገጥ ታሪኩ ግልጽ ነው። የወንጌላቱ ዓላማም በግልጽ ይነበባል፤ ይህም ወደ ነፍሳችን እረኛና ጠባቂ፥ ወደ ዓለም መድኃኒት የሚያመለክት ነው። የታሪክ ማእከልና እንብርት ወደሆነው በመስቀሉ ላይ ወደተፈጸመው ድንቅ የእርቅ ሥራ የሚያመለክት ነው። ይህ ክብርም፥ ምስጋናም፥ አምልኮም፥ ስግደትም፥ ውዳሴም ለሌላ ለማንም ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለእግዚአብሔር ብቻ መሆን እንዳለበት ያሳየናል።

ለእግዚአብሔር ብቻ ካልሆነ በቀር ለአምላክ የሚሰጥ ማናቸውም ነገር ለሌላ ፍጡር መሰጠት የለበትም። ማርያም የጌታችን እናትም እንኳ ብትሆን የአምላክን ክብር ቆርሰን ልናቀርብላት አልታዘዝንም። ጌታ አላዘዘንም፤ ሐዋርያትም አላስተማሩንም። በዘመናችን እንደሚታየው የመሰለ የገነነ አፍቅሮተ ማርያምና አምልኮተ ማርያም አስፈላጊ ቢሆን ኖሮ ምነው ጌታ እናቱ ወደ እርሱ እንዳመለከተችው እርሱም ወደ እርሷ አላመለከተም? ሐዋርያትስ ከሰፊና ጥልቅ ትምህርታቸው ምነው ይህን አላስገቡም? የለም፤ ይህ ደሓራዊ ትምህርት ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ በቀጥታም በርቀትም የማይገኝ የኋላ ስሕተት ነው። ከአንዱና ብቻውን ከሆነው አምላክ በቀር ለሌላ ስግደትና አምልኮን፥ ውዳሴና ምስጋናን መስጠት ጣዖትን ማምለክ ነው። ኢሳ. 42፥8 *እኔ እግዚአብሔር ነኝ ስሜ ይህ ነው ክብሬን ለሌላ፥ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም* ይላል። እግዚአብሔር ክብሩንም ምስጋናውን ከማንም ጋር አይጋራም።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ እናት ማርያም የሚናገረውና የማርያም አምላኪዎች የሚናገሩትና የሚያስተምሩትና የጻፉት ሁሉ በወንጌላት ውስጥ ከተጻፈችው ማርያም የተለየ ነውና ሌላ ማርያም እንጂ ያቺ ማርያም ናት ማለት አይቻልም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናያትና ታሪኳን የምናነብበው ማርያም ጨዋና ስፍራዋን በትክክል ያወቀች ሴት ናት። በካቶሊክ እና በኦርቶዶክስ ሃይማኖት የምናያት ማርያም እርሷ የምትፈልገው ሁሉ የሚደረግላትና በእግዚአብሔር ያለምንም ጥያቄ የሚፈጸምላት እመቤት ናት። መድኃኒትና መዳንም አያስፈልጋትም፤ ምክንያቱም ከጥንተ አብሶም፥ ከጎልዮ ኃጢአትም፥ ከግብር ኃጢአትም ሁሉ ነጻ ናት። ከኃጢአት ነፃ ሆና የተጸነሰች ናት። ወላጆቿም ሆኑ የዘር ሐረጓ በጠቅላላው ከአዳማዊነት የጸዳ የተለየ ሐረግ ካልሆነ ከዚህ እንዴት ነጻ ልትሆን እንደቻለች ድንቅ ነው። እርሷ በወንጌላት ውስጥ የምናያት ማርያም ግን በሉቃ. 1፥47 *ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤* ያለች የጌታ አክባሪ፤ መንፈሷ በመድኃኒቷ በአዳኟ ሐሴት ያደረገች፥ አዳኝና መድኃኒት እንዳስፈለጋት የተረዳች ናት። ኃጢአተኛ ሰው ሆኖ አዳኝ የማያስፈልገው ከቶ ማን ነው? ማርያም ስለ ራሷ እንዲህ ከመሰከረች እርሷን እንስማ ወይስ ስለ እርሷ የሚናገሩት ሌሎች የሚሉትን እንስማ? ከባለቤት ያወቀ ቡዳ ነው ይሏል ይህ ነው። ስለ አንድ ሰው እና ያንን ሰው ከእግዚአብሔር ቀጥሎ የሚያውቅ ያ ሰው ራሱ ነው። ሌላው ሁሉ የሚያውቀው እውቀት ከዚያ ሰው ያነሰና ያ ሰው ከገለጠው የተከፈለ ብቻ ነው። ለዚህ ነው ማርያምን ወይስ ስለ እርሷ ከብዙ መቶዎች ዓመታት በኋላ የጻፉ ሰዎችን እንስማ ያልኩት።

እመቤት ማለትም የጌታ እኩያ ነው። ጌታን ጌታችን እንደምንል ሌላ ሰውን ጌታችን ብንል ስሕተት እንደሚሆን እርሱን ጌታ በምንልበት መልክ ሌላ ሴትን እመቤታችን ብንልም ያው ነው። እግዝእትነ ማለት በአንስታይ ጌታ የማለት አቻ ነው።

# ወላዲተ አምላክስ?

በኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖት ማርያም ወላዲተ አምላክ ናት። ስያሜው ግዙፍ ነው። ቃሉ ወይም ስያሜው የተጀመረው በ4ኛው መቶ ምዕት ዓመት ስለ ክርስቶስ ማንነት በተፈጠረው ክርክር ወቅት ነው። በኒቅያው ክርክር ሆኖበት የክርስቶስ መለኮትነት በተረጋገጠበት ጉባኤ ማርያምም የመለኮት ተሸካሚ (ቴኦቶኮስ) መሆኗ ተብሎ በ431 የኤፌሶን ጉባኤ ተቀባይነት ያገኘ ስያሜ ነው። ስያሜው ግን በማርያም ማንነት ሳይሆን የዚያ ዘመን አከራካሪ ጉዳይ በነበረው በክርስቶስ ማንነት፥ ማለትም፥ አምላክ እና ሰው ብሎ የመለየቱ ክርክር ላይ ያተኮረ ነው።

በድንግል ማርያም ማኅጸን ያደረው ሥጋን የነሳው ጌታ ሰው የሆነው ጌታ ሆኖ ጌታ የነበረውና ሆኖ የኖረው ነው። ኤልሳቤጥ ማርያምን የጌታዬ እናት ማለቷ እውነት ነው። በማርያም ውስጥ የነበረው ጌታ ነው። መልአኩ ገብርኤልም ልዩ ሰላምታ ማቅረቡም በሉቃስ ወንጌል ተጽፈዋል። አንድ መጽሐፍ ሰዎች ይህን የመልአኩ ገብርኤልንና የኤልሳቤጥን ምስጋና ማቅረብ የተገባ ስለመሆኑ የኤልሳቤጥን ሰላምታ፥ “ምንኛ አስደናቂ ውዳሴ ነው” ሲል የገብርኤልን ሰላምታም ምስጋና በማለት፥ “እመቤታችን የተመሰገነችው በሰዎች ብቻ ሳይሆን በመላእክትም ነው” ይላል።[2] ነገሩ ውዳሴና ምስጋና ሳይሆን ሰላምታ መሆኑን መገንዘብ አይከብድም። ማርያም ለገብርኤል ምላሽ ስትሰጥ፥ “ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው?” አለች እንጂ፥ “ይህ እንዴት ያለ ውዳሴና ምስጋና ነው!” አላለችም። ደግሞም፥ “በሰዎችና በመላእክት” የሚለውን አጋኖ እናስተውል። ገብርኤል አንድ መልአክ፥ ኤልሳቤጥም አንዲት ሴት ናቸው። ደግሞም ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ፥ ኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞልቶባት የተናገሩት ሰላምታ ነው። ይህ የቀረበ የአንድ ጊዜ ሰላምታ ማርያም በሕይወት ሳለችም ከሞተች በኋላም አልቀጠለም፤ መቀጠልም የለበትም፤ ሊቀጥልም አይችልም፤ በአካል የለችምና። ሳለች እንኳ በሉቃ. 11፥27-28 አንዲት ሴት፥ *የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው* ስትል ጌታ፥ “እውነትሽን ነው” አላላትም። *ያላት፥ ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው ነው።*

ትውልድ ሁሉ ግን ብጽዕት ማለታቸው ይቀጥላል። ይህ ምስጋናና ውዳሴ ወደ እርሷ ማቅረብ ሳይሆን የሆነችውን ኹነት መናገር ነው። በወንጌል የተጻፈ ለማርያም የቀረበ ሌላ ሰላምታም ሆነ ምስጋና ባይኖርም ይህ ከላይ የተጠቀሰውን የጻፈ ጸሐፊ በነጠላ ሳይሆን በብዙ እንዲህ ጽፎታል። የዚህ ጸሐፊ አቀራረብም ከዲቪዲው የተለየ አይደለም፤ ትኩረቱ በዶክተር ቶሎሳ ስብከት ላይ ሲሆን ወንጌላውያን አማኞችን የፈረንጅ ፍርፋሪ ለቃቃሚ ይላቸዋል። ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች የሕይወትን እንጀራ የበሉ ናቸው እንጂ የፈረንጅም የአበሻም ቅራሪና ፍርፋሪ ለማኝ እንዳይደሉ ድፍን ካልሆነ በቀር በአሜሪካ የሚኖረው የሰውሩ ሊደጋ ጸሐፊ ልቡናም ያውቀዋል። አገር ቤት ተቸግረን ፍርፋሪ የበላን ቢመስለው እኅኑ ያሉት ጎረቤቶቹስ? በሒስ ውስጥ የቋንቋ ጨዋነት ቢኖር መልካም ይመስለኛል።

ወደ ነጥቤ ስለመስ፥ ወላዲተ አምላክ ሲባል እርግጥም ስያሜው ግዙፍ ነው። ማርያም ኢየሱስ መለኮት እያለ ሥጋን የነሳባት እናቱ ናት እንጂ የመለኮትነቱ ወላጅ አይደለችም። መለኮት አይወለድም። እመ አምላክ ወይም ወላዲተ አምላክ ሲባል እንደሚታወቀው ማንም ልጅ ከእናቱ

---

[2] *ሰውሩ ሊደጋ፥ ገጽ 100-101።*

በፊት ሊኖር አይችልምና ፥ የእናቱም ኋላኛና ተከታይ ነውና መገኘቱ ደሐራዊ ነው። እግዚአብሔር ዘላለማዊ አምላክ ነውና ማርያም እግዚአብሔርን አልወለደችም። ይህ ማለት፥ ማርያም እግዚአብሔርን አልወለደችም እና ኢየሱስ አምላክ አይደለም ማለት አይደለም። ማርያም ከመለኮት ቀዳሚነት እንደሌለባት ሁሉም የሚቀበለው ቢሆንም ሹመቱ ለማያስተውል መለኮታዊ ክብርንና ውዳሴን የሚያቀዳጅ ነው። ማርያም ያደረገችው ወይም የሆነችው ነገር ከዘላለም የነበረው ቃል፥ እርሱም እግዚአብሔር ወልድ፥ ሥጋን እንዲነሳ፥ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ እንዲያድር ራሷን ያዘጋጀችና መመረጧንም የተቀበለች ሆና መገኘቷ ነው።

## ቤዛዊተ ኲሉ ዓለም እና እመብርሃንስ ናት?

"የመዳናችን ምክንያት፥ ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገርንባት መሰላል፥ የአዲስ ኪዳን ኪሩብ" ይላታል የመምህር ምሕረተአብ ዲቪዲው መግቢያ። ዓለምን ያዳነች የተቤዠች ሆና ቀርባለች። መድኃኒት ናት፤ ነቢያትንና ጻድቃንን የምትዋጅ እመ ብርሃን፥ ቤዛዊተ ዓለም መሆኗ ይነገራል። ቤዛ ማለት የነፍስ ዋጋ ለነፍስ የሚከፈል ዎጆ ነው።

ስለ ቤዛነት የአዲስ ኪዳን ትምህርት ግልጽ ነው፤ ቤዛችን አንድ ብቻ፥ እርሱም በመስቀል ላይ የሞተልን ክርስቶስ ነው። ሌላ ቤዛ መኖሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጻፈምና በኋላ ከተፈጠረ ይህ ከቃሉ ጋር የሚጋጭ ስለሆነ ስሕተት መሆኑ ግልጽ ነው። ታዲያ ይህን ስሕተት መምህራኑ ስለምን ያስተምራሉ? ደሟን አፍስሳ የሰውን ልጅ እንዳዳነች የሚሰበክ የጌታ ደም የእርሷ ንጹህ ደም በመሆኑ ነው ይሉናል።

*በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ፤ ሮሜ. 3፥24*

*በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት፤ ኤፌ. 1፥7*

*ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ፥ ይህም በገዛ ዘመኑ ምስክርነቱ ነበረ፤ 1ጢሞ. 2፥6*

*የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም፤ ዕብ. 9፥12*

*መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና፤ ሐዋ. 4፥12።*

የማርያም ሞት የሚያድነንማ ቢሆን ክርስቶስ መሞትም አያስፈልገውም እኮ ነበር። ይቅርና መሞት፥ ቀድሞውኑ መወለድም አያስፈልገውም ነበር። ማርያም ከኃጢአት ንጹሕ ሆና ከተወለደች እርሷ መሞትና በደሟ መንጻት አይቻለንም ነበር?

እመብርሃንስ? ይህም ጌታ የዓለም ብርሃን መሆኑን ተናግሮአልና የእርሱ እናት መሆኗን ገላጭ ይመስላል። ግን እግዚአብሔር የብርሃናት አባት እንደተባለ እርሷም የብርሃን እናት ስትባል ከማን ጋር እየተስተያየችና እየተካከለች መሆኗን እናስተውል። እግዚአብሔር የብርሃናት አባት ከሆነና ማርያም የብርሃን እናት ከተባለች እኩያነቱ ምን እየተደረገ ነው?

ማርያም ሌላው ሁሉ ማዕረግ ባይሰጣትና የጌታችን እናት ወይም የኢየሱስ እናት ብቻ ብትባል ምንም የሚጎድልባት ነገር የለም። ፈጽሞ የለም። ወ/ሮ የሺመቤትን እናውቃለን? ወ/ሮ የሺመቤት የተሰማ ወይም የአሸብር እናት ሊሆኑም ይችላሉ። እዚህ የምለው የራስ ተፈሪ ወይም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን እናት ነው። እኚህ ሴት የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሥዩመ እግዚአብሔር ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ እና ቢባሉ ወይም በኖሩበትና ተፈሪ መኮንንን በወለዱበት የኤጀርሳ ጎሮ ቋንቋ ሃ 'ራ ታፋሪ ቢባሉ በሰውነታቸው፥ በማንነታቸው ላይ የሚፈጥረው ምንም ለውጥ የለውም።

ስዕሎቹን አይተናል? የማርያም ስዕል በኦርቶዶክስም በካቶሊክም ሁሌም ሙሉ፥ ቆንጆ፥ ጠንካራ፥ ወዘተ፤ አብረው ባሉባቸው ስዕሎች ሁሉ ደግሞ ኢየሱስ ደካማ ወይም ሕጻን ወይም ከእርሷ ያነሰ ሆነው ይሳላሉ።

## እውን ማርያም አርጋለች?

ከላይ በአጭር እንደቃኘነው በካቶሊክ አስተምህሮ በ1950 የተቀነነው ቀኖና የምድር ኑሮዋ ዘመን ሲፈጸም ሳትሞት እንደ ሔኖክ ወደ ሰማይ ማረጓ ነው የተጻፈው። ስታርግ ደግሞ ሲያልን አራቁታ ነው የሄደችው። በኦርቶዶክስ ደግሞ በ64 ዓመቷ ሞታ ተቀብራ በ3ኛው ቀን ተነሥታ ማረጓ ተጽፎአል። በኦርቶዶክስ ይህን የሚመለከተው ተአምር በተአምረ ማርያም የተጻፈው (ተአምር 3 እና ተአምር 6) እርስ በርስ ይቃረናል። ተአምር 3 አይሁድ ሐዋርያቱ ሊቀብሩአት ሲወስዱአት ሬሳዋን ሊያቃጥሉ ሲደርሱባቸው ትተዋት መሸሻቸውንና ገብርኤል ከዮሐንስ ጋር ሥጋዋን ከሕይወት ዛፍ በታች አኑረው ነፍሷ ማረጓ ተጽፎአል። የሕይወት ዛፍ በምድር ይሁን ከምድር ውጭ አልተነገረም። በተአምር 6 ደግሞ አልሸሹም፤ አልጣሏትም፤ አልቅሰው፥ እጅ ነስተው በጌቴሴማኔ ቀበሩአት እንጂ ይላል። የቱ ይሆን ትክክል? ይህ ከሺህ 500 ዓመታት ያህል በኋላ የተደረሰ ድርሰት ነውና የቱም ትክክል አይደለም። መጽሐፉ ልብ ወለድ መሆኑ በግልጽ ይታያል፤ የልብ ወለድ መጽሐፍ መለኪያዎችንም ያሟላል።

ሰዎች ልብ ወለድ ጽሑፎችን እንደ እውነት የሚቀበሉበት ዘመን ላይ እንገናለን። በ1990ዎቹ የዳን ብራውን The DaVinci Code መጽሐፍ በወጣ ጊዜ የፈጠራ ጽሑፎችን ማንበብ ስለምወድ አንሥቼ በችኮላ ቃኘሁት። ስላልሳበኝ ተውኩት። ከ10 ዓመታት በኋላ ሰዎች ወደውት፥ ትልቅ ሲኒማ ሆኖ ተሠርቶ፥ እንደ እውነት አድርገው ተቀብለውት፥ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ደብቃ ያኖረችው ምስጢር አፈትልኮ እንደወጣ፥ ኢየሱስ ሚስት እንደነበረችው፥ ልጆች እንደነበሩት፥ ዝርያዎቹ አሁንም በአውሮጳ መኖራቸው እውነት መሆኑ ሲነገርና ያነበቡትና ያዩት በደም ፍላት ሲከራከሩ መጽሐፉን አነበብኩት። ሳነብበውም አሁንም ያው ልብ ወለድ ነው። ግን እውነትን ለማወቅ ያልወደዱ ሰዎች፥ እውነትን የተቀሙ ሰዎች ሐሰትን እውነት ብለው ይቀበላሉ።

ተአምረ ማርያም ዕርገቷን (በተአምር 7) ከእጸ ሕይወት ስር አስነሥቶ እንዳሳረገው ስለሚናገር አሁንም ግጭት አለበት። የተነሣችው ከ ጌቴሴማኔ ካልሆነ የተቀበረችው ጌቴሴማኔ አይደለምና ይህም ውስብስብ ሊፈታ ያስፈልጋል። በእውነቱ ይህ የሚፈታ ልቃቂት ሳይሆን ሊቀበሉት ሳይሆን ሊጠየፉት የተገባ መድኃኒታችንን፥ ቤዛችንን፥ ጌታችንን ለመሸፈን የተፈጠረ እኩይ ሥራ ነው። ለማርያም የሚሰጣትን የቆየውንም ዘመናዊውንም አድናቆተ ማርያም ወደ አምልኮተ ማርያም የቀየረ ሥራ ነው። በተአምር ተጸንሳ በተአምራት የተንቆጠቆጠ ኑሮ ኖራ በቤዛነት ሞታ በክብር ካረገች ከጌታ ክርስቶስ ምን አነሰች? ይህ ለማርያም የተሰጠ ስፍራ ከአክብሮት ያለፈ በመሆኑ የጣዖት አምልኮ ነው። የእግዚአብሔር ክብር ከእርሱ ተቀንሶ ለማንም ሊሰጥ የተገባ አይደለም።

በክፍል ሁለት ይቀጥላል . . . *ዘ. መ* *© 2012 (፪ሺህ፬) ዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት*

ዕዝሊ ezralit@gmail.com ቁጥር ፲፩ - ጥር ፪ሺህ ፬ ዓመተ ምሕረት JANUARY 2012

# እንደሚገባ ኑሩ

**ይሁን እንጂ፥ መጥቼ ባያችሁ ወይም ብርቅ፥ በአንድ ልብ ስለ ወንጌል ሃይማኖት አብራችሁ እየተጋደላችሁ፥ በአንድ መንፈስ እንድትቆሙ ስለ ኑሮአችሁ እሰማ ዘንድ፥ ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ ኑሩ። በአንድም ነገር እንኳ በተቃዋሚዎች አትደንግጡ፤ ይህም ለእነርሱ የጥፋት፥ ለእናንተ ግን የመዳን ምልክት ነው፥ ይህም ከእግዚአብሔር ነው፤ ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና፤ ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም፤ በእኔ ያያችሁት አሁንም በእኔ እንዳለ የምትሰሙት፥ ያው መጋደል ደርሶባችኋልና።**

**ፊል. ፩፥፳፯-፴**

በፊልጵስዩስ ከተማ ቤተ ክርስቲያን እንድትተከል መሳሪያ የሆነው ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መልእክት ሲጽፍ በእስር ቤት ውስጥ ሆኖ ነው። እርግጥ ተፈትቶ ሊያያቸው ተስፋ አድርጎአል። ግን ተፈትቶ ቢያያቸውና በመካከላቸው ቢሆን ወይም ከሩቅ ሆኖ ስለ እነርሱ ቢሰማ የምዕመናኑ ሕይወት ተመሳሳይ እንዲሆን ምክርን ላከላቸው።

በዚህ ክፍለ ምንባብ ጳውሎስ አራት ዐበይት ነጥቦችን ሲያካፍላቸው እናያለን። ከአራት ሊያንሱም፥ ወይም ከሸነሸንናቸው ከአራት ሊበልጡም ይችላሉ።

## 1. ፖሊሱን ሳይሆን ሕጉን እንፍራ።

**ይሁን እንጂ፥ መጥቼ ባያችሁ ወይም ብርቅ. . .**

ቢቀርብ፥ መጥቶ ቢያያቸው፥ አብሮአቸው ቢሆን ወይም ቢርቅ፥ ከሩቅ ስለ እነርሱ ቢሰማ፥ አብሮአቸው ባይሆን ለወንጌል ሲሉ የሚኖሩት ኑሮ ተለዋዋጭ መሆን እንደሌለበት ነገራቸው። አንዳንድ ሰዎች ሕግን ሳይሆን ሕግ አስከባሪውን ይፈራሉ። ደንቡን ሳይሆን ፖሊሱን ማለት ነው።

ከዓመታት በፊት በየእሁዱ ጧት ከፈረንጆች ጋር አመልክና ከሰዓት ከአበሾች ጋር ወደማመልከባት ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ። አንድ ጧት በመኪናው እንዲያደርሰኝ መጋቢያችን የጠየቀልኝ ልጅ ዩጂን ይባላል። በጣም ፈጣን የሆነች የስፖርት መኪና ናት የነበረችው። እርሱም ከተመደበው የጎዳና ፍጥነት ወደ 30 ኪሎ ሜትር አስበልጦ ነበር ይነዳ የነበረው። በመንገድ ላይ ቆመው የተሽከርካሪ ፍጥነትን እየለኩ የሚያስቆሙና የሚቀጡ ፖሊሶች የሚይዙት ሬዳር የሚሉት መሣሪያ አለ። እየከነፍን ሳለን የዩጂን መኪና ውስጥ የተተከለ ሌላ መሳሪያ ደወለ። ያኔ ዩጂን ያንን መሣሪያ ዘግቶ፥ ፍጥነቱን ቶሎ ቀንሶ በጎዳናው መደበኛ ፍጥነት መንዳት ጀመረ። “ምንድነው ይህ አሁን የደወለው ነገር?” ብዬ ጠየቅኩት። ዩጂንም፥ “የሬዳር ጠቋሚ (radar detector) ይባላል፤ ይህ የሚነግረኝ በ3-4 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ፍጥነት ተቆጣጣሪ ፖሊሶች አሉ . . . አየሃቸው?” ብሎ እየነገረኝ ሳለ ፖሊሶቹን እያየናቸው አልፈን ሄድን። ሌላ ሁለት ኪሎ ሜትር ያህል ነዳና ጠቋሚውን መሳሪያ እንዲሠራ ከፍቶ እንደገና መክነፍ ጀመረ። ዩጂን ሕጉን የሚያከብር ሳይሆን ፖሊሶቹን የሚፈራ ሰው ነው። እስኪታየ ወይም እስኪተመሰገነ ድረስ ሕጉን ይጠብቃል፤ ካልታየ ግን ሕጉን ቢያጥፈውም፥ ቢቆለምመውም፥ ቢሰብረውም ደንታም የለውም።

አንዳንድ ክርስቲያኖችም እንደዚያ ነን፤ አይደል? እግዚአብሔር ሳይሆን ሰው አየኝ ወይስ አላየኝ የምንል ዓይነቶች ነን። ስለዚህ በሰዎች ፊት አንድ መልክ የያዝን፥ ለብቻችን ስንሆን ሌላ መልክ ያለን ቴያትረኞች ወይም ጭምብላሞች ሆነን እንኖራለን። እግዚአብሔርን ሳይሆን ሰዎችን ደስ የምናሰኝ፥ በሁለት አሳብ የምናነክስ ሥጋውያን ሆነን እንመላለሳለን። ጳውሎስ የፊልጵስዩስን ምእመናን የመከራቸው አብሮአቸው ሳይኖርም ልክ አብሮአቸው እየኖረ ቢያያቸው፥ ቢወቅሳቸው፥ ቢገስጻቸው የሚኖሩትን የመሰለ ኑሮ እንዲኖሩ መናገሩ ነው።

ጳውሎስ አብሮአቸው ባይሆንም በቅዱሳን ኅብረት ውስጥ ያሉ ወገኖች ናቸውና አንዱ ሌላውን የሚያይ ናቸው። ይህ አብሮ መጋደልንና አብሮ ወይም በአንድ መንፈስ መቆምን ይጠይቃል። ክርስትና በግል ከጌታ ጋር የመቆራኘት ሕይወት የመሆኑን ያህል የቅዱሳን ኅብረትን የሚጠይቅ አንዱ ሌላውን የማበረታታት፥ የማደፋፈር፥ አንዱ የሌላውን ሸክም የመሸከም ሕይወት ነው። የግል ግንኙነት፥ ግን የማኅበር ጉዞ ነው። በዚህ የማኅበር ጉዞ አንዱ የሌላውን አካሄድ የሚያይበትም ነው። ይህ እንደሚገባ መኖር ሩቅ ያለውን አገልጋይ ብቻ ስሳይሆ፥ ወይም ሕጉን ሳይሆን ፖሊሱን የሚፈሩ በሚፈሩበት መልኩ ሌላውን አማኝ በመፍራት ሳይሆን ግድ ተሰምቶን በግልጽነት እየታየን፥ እየተፈተሸን የምንጓዝበት አመላለስ ነው።

## 2. እንደሚገባ እንኑር (የተገባውን ያህል እንኑርለት)

**በአንድ ልብ ስለ ወንጌል ሃይማኖት አብራችሁ እየተጋደላችሁ፥ በአንድ መንፈስ እንድትቆሙ ስለ ኑሮአችሁ እሰማ ዘንድ፥ ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ ኑሩ።**

እንደሚገባ (ἀξίως- አክሲዮስ) የሚለው ቃል በዐረፍተ ነገር ውስጥ ቃሉ ከተነገረለት ባለቤት ጋር በጣም የተቆራኘ ነው። ያ ባለቤት የተገባው ሆኖ በመገኘቱ ለዚያ ሲባል የሚደረግ ነገርን መግለጫ ነው። ቃሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በርካታ ቦታዎች የተጻፈ ነው፤ አንድ ሁለቱን ለምሳሌ ብናይ፥

- ኤፌ. 4፥1 *በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ፤* መጠራታችሁ ክቡር ነውና ለዚያ መጠራት የተገባውን አመላለስ ተመላለሱ ማለቱ ነው።

- 1ተሰ. 2፥11-12 *ወደ መንግሥቱ ወደ ክብሩም ለጠራችሁ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ . . .* መጠራቱን ጥሪ ያደረገው ጠሪው ከጥሪውም በላይ የተገባው ነውና ጠሪውን የሚወክል የወኪል የሆነ፥ አገባብ ያለው፥ ግቡዕ አመላለስ ተመላለሱ ማለቱ ነው።

እዚህ እንደሚገባ ኑሩ የተባለለት የክርስቶስ ወንጌል ነው። ወንጌል በክርስቶስ የመስቀል ሞት በኩል ኃጢአተኞቹና ሞት የተገባን እኛ የእርሱን ጽድቅ ያገኘንበት መልካም ዜና ነው። ዋጋ የተከፈለበት ነውና እንደተከፈለበት ዋጋ መጠን ኑሮአችን ያንን ማንጸባረቅ አለበት። “ይገባዋል” ብለን ለዚያ ለተገባው ለመኖር የምንከፍለው ዋጋ ነው።

ልጅ ሳለሁ ከልጆች ጋር ሆነን የምናደርጋቸውን አጓጉል ጥፋት አንዳንድ አዋቂዎች አይተው፥ ‘ምን ነካህ? አንተ የእገሌ ልጅም አይደለህ?’ ወይም፥ ‘እንዴት የነ እገሌ ቤተ ሰብ ሆነህ እንዲህ ያለ አሳፋሪ ነገር ትሠራለህ?’ ያሉን ጊዜ አለ? ‘የእገሌ ልጅ ወይም የነ እገሌ ቤተ ሰብ ሆነህ እነርሱን የሚያሳፍር፥ ስማቸውን የሚያጎድፍ አሳፋሪ፥ ነውረኛ ነገር ለምን ታደርጋለህ?’ ማለታቸው ነው። ያደረግነው ሥራና የወላጆቻችን ወይም የቤታችን ስምና ክብር አይመጣጠንም ማለት ነው። ክብረ ነክ፥ ስም አጉዳፊ፥ አሰዳቢ፥ አሳፋሪና ነውረኛ ነገር አድርገናልና፥ ‘እገሌ እንዲህ አደረገ’ ሳይሆን፥ ‘የእገሌ ልጅ ወይም የነ እገሌ ወንድም እንዲህና እንዲህ አደረገ’ ይባላል።

ኢሳ. 52፥5ን ጠቅሶ ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 2፥24 *በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባልና ተብሎ እንደ ተጻፈ* ብሎ እንደጻፈው አይሁድ ለእግዚአብሔር ስም መሰደብ ምክንያት እንደሆኑ ያኔ የፊልጵስዩስ ምእመናን፥ ዛሬ ደግሞ እኛም ወንጌሉ እንዳይሰደብ ኑሮአችንና አመላለሳችን ለወንጌሉ የተገባ መሆን ይጠበቅበታል።

የክርስትና አመላለስ ክርስቶስን የመምሰል፥ እርሱን የመኮረጅ፥ የሆነውን ለመሆን፥ ያደረገውን ለማድረግ የመጣጣር ሂደት ነው። እርሱንም ለመምሰል በመንፈስ ቅዱስ የመደገፍ ውስጣዊ ግፊት ወይም መነሳሣት ነው። ይህ ጤማና ግፊት በቦታው ከኖረ ምንም ጉንተላ አያስፈልግም፤ ነገር ግን ሁሌ የማይኖርበት ወይም አንዳንዴ ከስፍራው የሚጠፋበት ጊዜ አለ። ያኔ ቆም ብሎ በሌሎች የምንታይ የሌላ ወኪሎች መሆናችንን ማወቃችን አስፈላጊ ነው። አንድ የሕዝብ ወኪል የሆነ እንደራሴ ወይም የመንግሥት ወኪል የሆነ አምባሳደር ያለበትን ስፍራና ሁኔታ ይወድደውና ይስማማ ይሆናል። አብረውት ያሉት ብዙዎች ተስማምተው የሚወስኑት ወይም የሚያደርጉት ነገርም ይስማማው ይሆናል። ነገር ግን የራሱን ስሜት ወይም በዙሪያው ያሉትን ሰዎች የማስደሰት ሳይሆን ለራሱ ባይስማማውም እንኳ የወካዩን ሕዝብ ወይም መንግሥት ድምጽና ውሳኔ ማንጸባረቅ ይጠበቅበታል። ይህ ለላከውና ለወከለው አካል የተገባ አመላለስ ማለት ነው። ለወንጌል የተገባ አመላለስ የኛን አመላለስ ሌሎች አይተው ወንጌልን የሚወድዱበት፥ ጌታን የሚቀበሉበት አመላለስ ነው።

አኗኗርና አመላለሳችን ለወንጌልና ለጌታ ስም መሰደብ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ሁሉ ለስሙ ክብርና ለሌሎች መስህብ ሊሆንም ይችላል።

## 3. ተቃውሞ የመዳን ምልክት ነው

**በአንድም ነገር እንኳ በተቃዋሚዎች አትደንግጡ፤ ይህም ከእነርሱ የጥፋት፥ ከእናንተ ግን የመዳን ምልክት ነው፥ ይህም ከእግዚአብሔር ነው፤**

ጳውሎስ ወንጌልን በሰበከ ጊዜ በፊልጵስዩስ ጠንካራ ስደት ተፈጥሮ ነበር፤ የተቃውሞው ዝናብ አንዴ ወርዶ ከዚያ አላባራም። የፊልጵስዩስ ምእመናን እንደ ሌሎቹ ክርስቲያኖች ሁሉ የማያምኑ ሰዎች ከሚያደርሱባቸው ስደትና መከራ የራቀ ሕይወት ሊኖሩ ተቃውሞና መከራው ያለ ነገር ነውና በመደንገጥ ፈንታ መደላደል እንዳለባቸው ጻፈላቸው።

ተግባራዊ ክርስትና ተቃውሞ መታወቂያው የሆነበት ኑሮ ነው። የመዳናችን ምልክትና ምስክርም ነው። ከክርስቶስ ወንጌል ወዲህም ሆነ ከዚያ በፊት እግዚአብሔርን መምሰልንና መከተልን የሰበኩ ብዙዎች ተሰድደዋል። እግዚአብሔርን መምሰል በጎ ከሆኑት ነገሮች ሁሉ በላይ ቢሆንም ይህ ለወደቀው አዳማዊ ባህርይ የሚመች አይደለምና አይፈለግም። ይህን ጽድቅ የሚሰብኩቱ ነቢያትም፥ የሌሎችን ሕይወት በንጽጽር የሚያስነቅፍ ንጹሕ ኑሮ የሚኖሩቱ ቅዱሳንም የተቃውሞና የስደት ጊጤዎች ይሆናሉ።

ስለዚህ የንጽሕና ሕይወት ተቃውሞ ማስደንገጥ የለበትም ማለት ነው። ክርስቲያን ክርስቲያን ስለሆነ ብቻ ስደትና ነቀፌታ ሊደርስበት ይችላል። ጴጥሮስ በስደት ውስጥ እያለፉ ያሉ ክርስቲያኖችን እንዲህ አላቸው፤ *ከእናንተ ማንም ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ክፉ አድራጊ እንደሚሆን ወይም በሌሎች ጉዳይ እንደሚገባ ሆኖ መከራን አይቀበል፤ ክርስቲያን እንደሚሆን ግን መከራን ቢቀበል ስለዚህ ስም እግዚአብሔርን ያመስግን እንጂ አይፈር፤* 1ጴጥ. 4፥15-16። እነዚህ ክርስቲያኖች መንግሥትን ተቃውመው ወይም ሰውን በድለው ስደት ቢደርስባቸው ሳይሆን ክርስቶስን ስለተከተሉና እርሱን ስለመሰሉ መከራን ቢቀበሉ ይህ እንግዳ ነገር መሆን የለበትም።

የስደትንና የቅጣትን ልዩነት አንጥረን ከተረዳን ስደትንና ተቃውሞን መቀበል አይከብድም። ቅጣት መጥፎ አድርገን በጥሩ ሰዎች የሚደርስብን ዋጋ ነው። ስደት ግን መልካም አድርገን በመጥፎ ሰዎች የሚደርስብን መከራ ነው። ተቃውሞ ከዓለም ጋር አለመመሳሰላችን ነው። ከወንዙ ጋር አንፈስስም፤ ከቆሻሻው ጋር አንጠረግም ማለታችን ነው። ከጅምሩና ከክርስቶስም ጀምሮ ተቃውሞ የነበረ ነው። ደቀ መዝሙሩ ከመምህሩ አይበልጥምና የእርሱ ተከታዮች ከተቃውሞ የራቀ ኑሮን አልኖሩም። እኛም ከዚያ የተሻለ ነገር መጠበቅ የለብንም።

አንድ ወንድም ጌታን ጌታው አድርጎ ከመከተሉ በፊት የጠፉና የከፉ ነገሮችን ሁሉ የሚያደርግ ወጣት ነበረ። ሰክሮ እቤት መጥቶ ይረብሻል፥ ይለፋደዳል፤ ገንዘብ ይሰርቃል፥ ጫት ይቅማል፥ ሐሺሽ ያጨሳል፥ ያመነዝራል፥ ዝርዝሩ ብዙ ነው። ጌታን ሲያገኝ አደበ፤ ሰላማዊ ሰው ሆነ፤ ቋንቋው ተለወጠ፤ ጎበዝ ተማሪ፥ ታዛዥ ልጅ፥ ታታሪ ሠራተኛ ሆነ። የገዛ ወላጆቹ ግን ከቤት አባረሩት። ተቃውሞ ብቻ አይደለም፤ ስደትም አለ።

## 4. ከስደት የጸዳ ሕይወት ተስፋ አልተገባም

**ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና፤ ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም፤ በእኔ ያያችሁት አሁንም በእኔ እንዳለ የምትሰሙት፥ ያው መጋደል ደርሶባችኋልና።**

ክርስትናን ከድሎትና ከምቾት፥ ከአዱኛና ብልጽግና፥ ከሥጋዊ ስኬትና ጤንነት፥ ከመንቀባረርና ከመንፈላሰስ ብቻ ጋር አቆራኝተው የሚያይዩና የሚያስተምሩ ሰዎች በዘመናችን በዝተዋል እንጂ አላነሱም። እነዚህ በረከቶች የምድራዊ ኑሮ ዘመናችን በረከቶች ናቸው እንጂ የክርስትና መታወቂያ ካርዶች አይደሉም። ምርቃቶች እንጂ ዋናው እሴቶች አይደሉም። *እነዚህም ምልክቶች ይከተሉአቸዋል* የተባሉልን ምልክቶችም አይደሉም።

እንደ ክርስቲያን ሆነን ሳንሳቀቅ ተረጋግተን በነጻነት የምንመላለስበት፥ ለመመስከርና እምነታችንን ለማካፈል፥ ለመሰብሰብና ለማምለክ፥ አካላችንም ኅሊናችንም ነጻ ሆኖ ጌታን የምናመልክበት መብት ባለን አገር የምንኖር ከሆንን እግዚአብሔር ይመስገን።

እንዲህ በመሰለ አካላዊና ከባቢያዊ ምቹ ሁኔታካልኖርንም እግዚአብሔር ይመስገን። ዛሬ በብዙ ኢ-ክርስቲያናዊ አገሮች የጌታ ልጆች እያለፉባቸው ያሉበት መከራና ስደት፥ ስቃይና ሞት የጨመረ እንጂ ያነሰበት ዘመን አይደለም። ይህን መጣጥፍ በምጽፍበት ወቅት (2011) ስለ እምነታቸው ነፍሳቸውን የሚሰዉ ክርስቲያኖች አማካዩ ቁጥር በዓመት 200 ሺህ ነው! በዓለማችን በ60 ያህል አገሮች የሚገኙ 200 ሚሊዮን ያህል ክርስቲያኖች መሠረታዊ የእምነትም፥ ከእምነታቸው የተነሣ የሰውነትም መብት የተነፈጉ ናቸው።[3]

ይህ አዲስ አይደለም። በክርስቶስ የተጀመረ ነው። ጳውሎስም ራሱ ከአሳዳጅነት ወጥቶ ለጌታው ያደረ ሲሆን ገና ከጅምሩ ነው ስደት የደረሰበት። እዚህም እያለ ያለው ይህን ነው፤ ***በእኔ ያያችሁት አሁንም በእኔ እንዳለ የምትሰሙት፥ ያው መጋደል ደርሶባችኋልና።*** በእርሱ የታየው መከራ ተካፋዮች እየሆኑ ናቸው የፊልጵስዩስ ምዕመናን። ጳውሎስ በእርግጥ መከራን ተቀብሎ ነው ከዚህች ከተማ የወጣው። በእኔ ያያችሁት ያለው በተግባር ያዩትን ስደትና እንግልት መናገሩ ነው። አሁንም እንዳለ የምትሰሙት ያላቸው በዚያን ጊዜ እያለፈ ያለበትን መከራ ነው። ይህ ደብዳቤ እየተጻፈ ያለው ከወኅኒ ቤት መሆኑን ቀደም ሲል አጥንተናል። 2ጢሞ. 3፥12 *በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ ይላል።*

* * * * *

*ዘላለም መንግሥቱ © 2012 (፪ሺህ፬) ዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት*

[3] *http://persecutedchurch.blogspot.com/2009/04/limits-of-statistics.html*

# የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ

*ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ፥ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ።*

ገላ. 4፥4-5

ለ2011 ገና ከገና በዓል በፊት ባለው እሁድ በቤተ ክርስቲያናችን የተካፈልነው ቃል ነው። በጽሑፍ ዋናውን አሳብ አቅርቤዋለሁ።

እግዚአብሔር ተስፋን ይሰጣል፤ የሰጠውን ተስፋም ይፈጽማል። ይህ በዚህ የተነገረው የተፈጸመ ተስፋ ነው። ተስፋው አዳምና ሔዋን በኃጢአት በወደቁ ጊዜ የተነገረው እግዚአብሔር በመጀመሪያ የሰጠውና ከሴቲቱ የሚወለደው የአሳቹን ራስ የሚቀጠቅጥ መሆኑን የተናገረበት ነው። ይህን ተስፋ እግዚአብሔር ጊዜውን ጠብቆ ፈጸመ። እንዲፈጸም የወሰነበት ዘመን ሲደርስ፥ በዘመኑ ፍጻሜ፥ ተስፋውን ከተስፋነት ወደ ተጨባጭነት፥ ወደ ተዳሳሽነት፥ ለወጠው።

## 1. መቼ? የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ

መጀመሪያ ዘመን የሚለውን አሳብ እንመልከት። እግዚአብሔር በዘመን ውስጥ የሚሠራ አምላክ ነው። እርሱ ከዘመን ውጪ ቢሆንም፥ ለእርሱ ዘመን የተፈጠረና ኋላ የመጣ ነገር ቢሆንም፥ ጊዜ ራሱ የተፈጠረ ነገር ቢሆንም፥ ከኛ ጋር ባለው ግንኙነቱ በዘመን ውስጥ ይሠራል። ለሁሉም ነገር ጊዜ አለው፤ መክ. 3። ከጊዜ ውጪ ስለሆነ ሲፈልግ ከጊዜ ጋር የሚጣሉ ነገሮችንም ያደርጋል፤ ለምሳሌ፥ በሕዝቅያስ ዘመን የጥላው ስፍረ ሰዓት ወደ ኋላ ተመለሰ፤ ኢሳ. 38፥8። በኢያሱ ዘመን ፀሐይ በነበረችበት ቆማ ቀረች፤ ጦርነቱ እስኪያልቅ፤ ኢያ. 10፥12።

ለኛ መዘግየት ወይ መፍጠን የሚመስሉን ሁኔታዎች ለእግዚአብሔር መዘግየትም መፍጠንም አይደሉም። እኛ በዘመንና በጊዜ ውስጥ የምንገኝ ስለሆንን ግን ከኛ ጋር ባለው ጉዳዩ በጊዜ ውስጥ ነው የሚሠራው። ሲታገስ ለሰው ልጆች ጊዜ እየሰጠ ነው። ያ ጊዜ የሚያልቅበት ጊዜ፥ ያ ዘመን የሚፈጸምበት ዘመን ደግሞ አለ።

ለምሳሌ፥ ዘፍ. 15፥12-16 የ400 ዓመት ትእግሥት! አራት ትውልድ! ዘሌ. 18 እነዚህ ሰዎች ምን ያህል የከፉ መሆናቸውን ይነግረናል፤ የወላጆችን፥ የዘመዶችን ኀፍረተ ሥጋ ይገልጡ ነበር፤ ወንድ ከወንድ ጋር ይተኛ፥ ሴትም ከሴት ትተኛ ነበሩ፤ ሰው ከእንስሳ ጋር ይረከስ ነበር፤ ልጆቻቸውን ለሞሎክ እያቃጠሉ ይሰዉ ነበር። ግን የጊዜ ገደብ ተሰጣቸው፤ 400 ዓመት!

*በእነዚህ ሁሉ ከፊታችሁ የማሳድዳቸው አሕዛብ ረክሰዋልና በእነዚህ ነገሮች ሁሉ አትርከሱ። ምድሪቱም ረከሰች ስለዚህ ኃጢአትዋን በእርስዋ ላይ እመልሳለሁ፥ ምድሪቱም የሚኖሩባትን ሰዎች ትተፋለች።* ቁ. 24-25። ለአብርሃም በተሰጠው ቃል መሠረት የአብርሃም ዘር ሕዝብ ሆኖ የቅጣት መሣሪያም ሆኖ ተመለሰ። ቅጣት ተፈጸመ።

በዘመኑ ፍጻሜም ልጁን ላከ። የላከው ያ ጊዜ ትክክለኛው ጊዜ ነው። ቀድሞ አልሆነም፤ ቆይቶ አሁን በዘመናችንም አልሆነም። የተቀጠረለት ቀን ነበረና በዚያ ጊዜ ሆነ። እግዚአብሔር በጊዜ ውስጥ ይሠራል።

- አንደኛ የግንዛቤ ነጥብ፤ በኛም ሕይወት እግዚአብሔር በጊዜ ውስጥ እንደሚሠራ ይግባን። በጊዜ ውስጥ እንዲሠራ ደግሞ ማድረግ ያለብን አንድ ነገር ጊዜን መስጠት ነው። ለግንኙነት ጊዜ፥ ለጸሎት ጊዜ፥ ለንባብ ጊዜ፥ ለማገልገል ጊዜ። በጊዜ ውስጥ እግዚአብሔር ይሠራል። በጊዜ ውስጥ እንዲሠራ ሌላው ማድረግ ያለብን መጠበቅ ነው። መቼም መጠበቅ ወይም መታገሥ የምትባለው ነገር ጭንቅ ናት። ስለ ትእግሥት አንድ መረዳት ወይም ማወቅ የተገባን ነገር መታገሥ ወይም ትእግሥት የኛ ጥረት ሳትሆን የመንፈስ ፍሬ መሆኗ ነው።

## 2. እንዴት? ከሴት የተወለደውን

ከሴት መወለዱ አስፈላጊና ተገቢ ነው። ቀድሞም ተስፋው የተሰጠው በሴቲቱ በኩል የሚመጣው ራሱን የሚቀጠቅጠው መሆኑን ነው፤ *በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።* ዘፍ. 3፥15

ተስፋው በቀጥታ ለሔዋን የተሰጠ ሳይሆን ፍርዱ ግን ለአሳቹ የተሰጠ ነው። በዚያ የፍርድ ቃል ውስጥ ነው ተስፋው የተነገረው። ከሴት መወለዱ ከአዳማዊ ኃጢአት የተለየ መሆኑን ነው። ኢየሱስ ከወንድ ከተወለደ ሰው፥ ወይም ኃጢአተኛ ሰው ብቻ እንጂ አምላክ ሊሆን አይችልም።

በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ በተጻፈው በኢየሱስ የትውልድ ሐረግ ውስጥ ከማርያም ጋር አራት ሌሎች ሴቶች ተጠቅሰዋል። በመጀመሪያዎቹ 6 ጥቅሶች ስማቸው የተጻፈልን እነዚህን ሴቶችና ታሪካቸውን ስንመረምር የሚያስመሰግንና የሚያስወድስ ታሪክ ያላቸው ሴቶች ከቶም አይደሉም።

- ትዕማር ማለት ይሁዳ ከገዛ ልጁ ሚስት መንታ ልጆችን የወለደባት ሴት ናት።
- ራኬብ የተባለችው ሴት በብዙ ትርጉሞች ረዓብ የተሰኘችው የኢያሪኮዋ ጋለሞታ ናትና ከጠፉት አሞራውያን ወገን ናት።
- ሩትም ፈጽሞ አይሁዳዊት አይደለችም፤ ሞዓባዊት ናት፤ በትውልድ ሐረጉ ውስጥ ግን ገባች።
- ቤርሳቤህ እንዲያውም የዳዊት ሚስት ሳትሆን የኦርዮ ሚስት ነው የተባለችው፤ ታሪኩ መጥፎ ነው።

የነዚህ አሳፋሪ ሴቶች ታሪክ ከንጉሡ ኢየሱስ ታሪክ ውስጥ ተቀርፈው አልወጡም። ሆን ብለው የተሳተ ሴቶች ናቸው። የኢየሱስን ታሪክ ከነዚህ ሴቶች አሳፋሪ ታሪክ ለማጽዳት የተደረገ ምንም ሙከራ አልኖረም። አላስፈለገምም።

ከሴት የተወለደውን ጌታ የወለደችው ከነዚህ ጋር የተጻፈችው ማርያምም ልዩ ፍጡር ሳትሆን በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ያገኘች፥ ልዑል ከእርሷ እንዲወለድ ራሷን ያሰናዳች ሴት ናት። ማርያም በትውፊትና የተፈጠሩ ተረቶች እንደሚባለው ያለኃጢአት የተጸነሰች፥ ከጥንተ አብሶ ወይም አዳማዊ ኃጢአት የነጻች አይደለችም። ብትሆን ኖሮ መድኃኒት ወይም አዳኝ አያስፈልጋትም ነበር።

የጳውሎስ አሳብ ከሴት መወለዱን ሲናገር ማርያምን ለማክበር ወይም ለማዋረድ ያደረገው ነገር የለም። የገለጠው የኢየሱስን ማንነት ነው። ለነገሩ አሁን በካቶሊክና በኦርቶዶክስ ሃይማኖቶች ውስጥ እንደሚነገረው ያለው ነገረ ማርያም ከቀድሞም የነበረ ቢሆን ኖሮ ማርያም በተጠቀሰችበት ሁሉ፥ እመቤታችን፥ አማላጃችን፥ ቅድስት ድንግል፥ ከአንዴም ሁለቴ ሦስቴ ድንግል የሆነች፥ ወላዲተ አምላክ፥

ቤዛዊተ ኩሉ፥ የኖኅ መርከብ፥ ያያዕቆብ መሰላል፥ ወዘተ ወዘተ፥ ማለት ነበረባቸው። ግን አላሉም። ጳውሎስ የገለጠው የኢየሱስን ማንነት ነው። የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ ተስፋ የተሰጠው የእባቡን ራስ ቀጥቃጭ እንደተሰጠው ተስፋ ከሴት መወለዱን መግለጡ ነው።

ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቂና የተገባት ስፍራ ተሰጥቶአታል። ማርያምም በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተጠቀሰችባቸው ጥቅሶች ሁሉ ውስጥ በማንነቷ የረካችና ደስተኛ እንጂ የሥልጣን ጥመኛ ሆና ወይም መስላ አልታየችም። የተጻፉትን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አይታ ወይም አንብባ ቢሆን ኖሮ እንኳ አንዳች ልትጨምርበት የምትፈልግ እንዳልሆነች ግልጽ ነው። መንፈስ ቅዱስን የምታውቅ ሴት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ወይም ነጂነት ለተጻፈ ቃል ከደስተኛነት በቀር ምን ሊኖራት? ለጌታ ሥራና ለኢየሱስ ሥጋ መልበስ ራሷን በንጽሕና የጠበቀች ሴት ናት።

- ሁለተኛ የግንዛቤ ነጥብ፥ ለእግዚአብሔር ሥራና አሠራር የተዘጋጀን ሰዎች ልንሆን ያስፈልገናል። በተዘጋጁ፥ በተሰናዱ ሰዎች፥ እንደ ማርያም 'እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ' በሚሉ ሰዎች ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር ጉዳይ አለው። ሥራ አለው። ክርስቶስ አንዴ ተወልዶአልና ዳግም አይወለድም። ግን የክርስቶስ አሳብ ይወለዳል፤ ራእይ ይወለዳል፤ አገልግሎት ይወለዳል፤ ታዲያ ለዚህ ምን ያህል የተዘጋጀን ነን? ምን ያህል ያመንን ነን? ምንስ ያህል ዋጋ ለመክፈል የተዘጋጀን ነን?

## 3. ሌላስ? ከሕግ በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤

ጌታ ከሕግ በታች ተወለደ። ጌታ የተወለደው በብሉይ ዘመንና ኪዳን ውስጥ ነው። አዲሱ ኪዳን እስከ መስቀሉ ድረስ ገና አልቆመም፤ አልተመሠረተምም። የጌታ ወንጌል አዲስ ኪዳን በምንለው መጽሐፍ ውስጥ ይጻፍ እንጂ ዘመኑ ገና የአሮጌው ኪዳን ዘመን መሆኑን እናስተውል። ጌታ የተወለደው ከሕግ በታች ነው።

*ማቴ. 5፥ 17 እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም* አለ። ማንም ሊጠብቀው ያልቻለውን መጠበቅ ጠበቀ። ፊደሉን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን የሕጉን መንፈስና፥ አሳቡንም ገለጠው (ማቴ. 5-7)።

ጳውሎስ ይህን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ ብሎ የላከላቸውን መልእክት የጻፈላቸው የገላትያ ሰዎች ናቸው። ገላትያ አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሳትሆን በእስያ የምትገኝ አውራጃ ናት፤ በውስጧም ብዙ ቤተ ክርስቲያኖችና ክርስቲያኖች አሉባት። የተፈጠረ የጎላ ችግርም ነበረባት። ያም፥ በጌታ ካመኑ በኋላ አንዳንድ ገያሪዎች (አይሁድ አድራጊዎች) ወደ ውስጣቸው ገብተው ወደ ሕግ ሥራ እንዲመለሱ፥ ሕግን በመጠበቅ እንጂ በጸጋ እንደማይድኑ ሌላ ወንጌል ሰበኩላቸው። እነዚህ የዋሆችም ፈጥነው ወደዚህ ወጥመድ ውስጥ ገቡ። በመንፈስ ጀምረው በሥጋ ሊጨርሱ ተሳሳቱ። ከመልካሙ ሩጫቸው ተንሸራትተው ወጡ።

ወደ ሕግ ሥራ እየተመለሱ ላሉ ለነዚህ ሰዎች ነው ይህንን ትልቅ እውነት የጻፈላቸው። ሕግን ጠብቀው መዳን ቢሆንላቸው ኖሮ ክርስቶስ ሥጋ መልበስና በመስቀል መሞት ባልኖረበትም!

- ሦስተኛ የግንዛቤ ነጥብ፥ ጌታ ያገለገለበትን ዘመንና የሕግን ምንነት አስተውለን እንገረዳ። እኛ ከሕግ በታች አይደለንም፤ እንዳንሆን ያደረገን ደግሞ ስለእኛ ከሕግ በታች ተወልዶ፥ ሕግን ሁሉ ፈጽሞልን፥ ከሕግ እርግማን የዋጀን ጌታ ነው። በመስቀሉም አዲሱን ኪዳን አቆመ። ስለዚህ ጌታን አጥብቀን እናመስግነው።

## 4. ለምን? ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ

ለምን? ይህ ሁሉ ለምን ሆነ? አይደንቅም እኛ ከሕግ በታች እንዳንሆን እርሱ ከሕግ በታች ተወለደ። ገላ. 3፥10 እና 13

*ከሕግ ሥራ የሆኑት ሁሉ በእርግማን በታች ናቸውና፤ በሕግ መጽሐፍ በተጻፉት ሁሉ ጸንቶ የማይኖር የማያደርግም ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና* (ቁ. 10)

*በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤* (ቁ. 13)።

ነጻነት፥ ቤዛነት፥ ዋጋ ይጠይቃል። ጌታ እኛን ከሕግ ቀንበርና እርግማን ነጻ ያወጣን ነፍሱን ከፍሎ ነው። ሕግ በራሱ ምንም ክፋት የለበትም፤ ጸጋው እንዲያድነን ኪዳኑ እስኪፈጸም በእምነት ወደ እግዚአብሔር መቅረቢያው ሆኖአል። አዲሱ ኪዳን በደም ሲመረቅ ግን ቦታውን ጸጋው በእምነት እንዲያድነን ለቀቀ። በጸጋው የመዳናችን ዋጋውም ደሙ ነው።

ከጌታ የመስቀል ሥራ ጋር በማይነጻጸር መልኩ የክርስትና አገልግሎትም ዋጋን የሚጠይቅ ነው። በ1ቆሮ. 9፥19-23 ሐዋርያው ጳውሎስ ለወንጌል ስለከፈለው ዋጋ ይናገራል። የሌሎች ነጻነት በዋጋ የተገኘ ነው። ይህንን የከፈለውን ዋጋ በ2ቆሮ. 11፥22-29 የገለጠበትን ቃል 'ፍርሃት' ይለዋል። ሌሎች ትርጉሞች ሌላ ቃል ይጠቀማሉ፤ ኢ.ት. አደጋ፤ መ.ት. አደጋ፤ ሕ.ቃ. አደጋ እና ችግር ይሉታል ልክ ነው፤ ቃሉ κινδύνοις ማለት፥ ስጋት ነው። ፍርሃት ሥጋት ወይም አደጋ ባለበት ሁኔታ ውስጥ በፍርሃት፥ በስጋት ማለፍን የሚያሳይ ቃል ነው። እንደዚህ ባለ ሁኔታ ነው ያገለገለው። አልከፈለም ዋጋ? ከፍሎአል።

በማስተምርበት ት/ቤት ጧት ጧት ብሔራዊ መዝሙር ይዘመራል፤ ይህ ሲሆን ሁሉም ምንም ሳያደርጉ ቀጥ ብለው ይቆማሉ። አንዱ ወጣጤ ልጅ ቆሟል፤ ግን በስልኩ የሆነ የውድድር ጨዋታ እየተጫወተ እንደመደነስም እያደረገው ተዘምሮ አለቀ፤ ሄድኩና ሁለተኛ እንዲያ እንዳያደርግ ነገርኩት፤ "ለምን?" አለ ቁብም ሳይሰማው። "ለነጻነትህ ትንሽ አክብሮትና አድናቆት ስጥ፤ እንዲህ እንድትሆን የበቃኸው ዋጋው የተከፈለ ነጻነት ስላለህ ነው፤ ሌላ ጊዜ የሕዝብ መዝሙር ሲዘመር 1ደቂቃ ከ15 ሰከንድ ብቻ ናትና ለዚያች ጊዜ ጸጥ ሳትል ባይህ ስልክህን እሳስረዋለሁ" አልኩት። የነጻነቱን ዋጋ ያላወቀ ሰነፍ ዜጋ!

ያ ብሔራዊ ነጻነት ነው። ሆኖም ለሌሎች የሚደረግ ነጻ የማውጣት ተጋድሎ ዋጋ ያስከፍላል። የኛ ከሕግ እርግማን አርነት መውጣት በዋጋ የተገኘ ነው። ይህ የተፈጸመው ከሕግ በታች መሆን የሌለበት እርሱ ለኛ ሲል ከሴት ተወልዶ፥ ከሕግ በታች ተወልዶ፥ በእንጨት ተሰቅሎ ከሕግ እርግማን ስለዋጀን ነው።

- አራተኛ የግንዛቤ ነጥብ፥ ለኛ መንፈሳዊ ነጻነት ዋናው ዋጋ በጌታ የተከፈለው ነው። ግን ሌሎችም ዋጋ ከፍለዋል። ወንጌልን የነገሩን፥ ያሳደጉን፥ ያስተማሩን ዋጋ ከፍለዋል። ጉልበት፥ ጊዜ፤ ገንዘብ አፍስሰዋል። ጌታ ሊዋጀን የሥጋና ነፍስ ዋጋ እንደከፈለ፤ እነዚህ ሰዎችም ዋጋ እንደከፈሉልን እኛስ ለሌሎች ዋጋ ለመክፈል የተዘጋጀ ልብ አለን? የከፈላችሁና እየከፈላችሁ ያላችሁ ጌታ ይባርካችሁ፤ ሽልማታችሁ፥ ዋጋችሁ በእጁ ነው፤ አንድ ቀን ከፊገግታው ጋር ትቀበሉታላችሁ። ሁላችንም ግን ለመክፈል የታጠቅን እንሁን።

በዚህ የልደት ሰሞን የተከፈለልንን ዋጋ ለማሰብ ጥቂት ጊዜም እንውሰድ።

ጌታ ከአርያም ይባርካችሁ።

* * * * *

*ዘላለም መንግሥቱ © 2012 (፪ሺህ፬) ዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት*